የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሀግብር

# በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና (በአፋር ክልል በዱብቲ እና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ አየለ ዘገየ

ሐምሌ፣ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና (በአፋር ክልል በዱብቲ እና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሀግብር


አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሑፍ


አማካሪ

ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር)

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ይህ "በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና (በአፋር ክልል በዱብቲ እና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአየለ ዘገየ የቀረበ ጥናት፣ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | | |
|---|---|---|
| ________________ | ________________ | ________________ |
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |

# ምሥጋና

በቅድሚያ እዚህ አድርሶ ይህንን ጥናት እንድሰራ የረዳኝ ሀያሉ ልዑል እግዚአብሄርን ምስጋና ይግባው። በመቀጠል ደከመኝ እና ሰለቸኝ ሳይሉ ያላቸውን ጊዜ በማጣበብ የጥናቱን ትክክለኛ አቅጣጫ በማሳየት ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ። ጥናቱን ስሰራ ከጎኔ በመሆን አስፈላጊውን የማቴሪያል እገዛ በማድረግ፣ በማበረታታት እና ጠቃሚ ምክሮችን በመስጠት ለረዱኝ ርዕሳነ መምህራን ለአቶ አህመድ ሀንፍሬ እና ለአቶ መንግስቱ ገ/መድህን ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመቀጠልም ይህን ጥናት በመጻፍ አስፈላጊውን እገዛ ላደረጉልኝ ለዱብቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፀሀፊ ለወይዘሪት ሩቅያ ትኩዬ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመጨረሻም  ለጥናታዊ ጽሑፍ መሳካት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ማመስገን እወዳለሁ፡፡

# አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአፋር ክልል ዱብቲና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድረሰት በሚፅፉበት ጊዜ ከፅሁፎቻቸው ውስጥ ስህተቶችን እና የስህተት ምንጮች ተለይተዋል፡፡ በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች የተመረጡትም ከእድል ሰጭ የንሞና አመራረጥ ዘዴ መካካል በቀላል የእጣ ንሞና (simple random sampling) ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ስራላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተጠኝ ተማሪዎች የተፃፉ ድርሰቶች፣ በተማሪዎቹና በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆች አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበው በስህተት ትንተና የአተናተን ዘደ መሰረት በአይነታቸው ተለይተው ተተንትነዋል፡፡ ከደርሰቱ እርማት በተገኘው መረጃ መሰረት አጠቃላይ የስህተቶቹ ብዛት 3526 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት 1803 (51.13%)፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም 1034 (29.3313%)፣ የቋንቋ አወቃቀር 577 (16.36%) እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች 112 (3.18%) ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከፃፏቸው ድርሰቶች፣ በተማሪዎችና በመምህርን ከተሞሉ መጠይቆች በተገኙ መረጃዎች መሰረት ዋናዎቹ የስህተት ምንጮች፡- ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የማስረፅ ስልት፣ ስነልቦናዊ እና የአማርኛ ቋንቋ ድምጸልሳናት ተፅዕኖ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ተማሪዎች ሆሄያትን አንደኛ ደረጃ ላይ እያሉ በትክክትል እንዲለዩ ቢደረግ፣ ለቋንቋ ትምህርት በቂ ክፍለ ጊዜ ቢሰጥ፣ መምህራን ተማሪዎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ ስለቋንቋው ጠቀሜታ አስፈላጊውን ግንዛቤ ቢፈጠሩ እና ትምህርቱ በ12ኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና እንዲሰጥ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሁኔታዎችን ቢያስተካክል የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦች በአጥኚው ተጠቁመዋል፡፡

# የይዘት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምሥጋና ........ i
አጠቃሎ (Abstract) ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ አላማ ........ 3
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.6. የጥናቱ ውስንነት ........ 4
1.7. የቁልፍ ቃላት ስያሜዎች ........ 4
ምዕራፍ ሁለት ........ 5
ክለሳ ድርሳናትና የቀደምት ጥናቶች ግኝት ........ 5
2.1. የድርሰት ምንነት ........ 5
2.2. የስህተት ምንነት ........ 5
2.3. የስህተት ትንተና ........ 7
2.4. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ ........ 8
2.5. የስህተት ምንጮች ........ 8
2.5.1 የውስጥ ቋንቋ ተፅእኖ ........ 9
2.5.2 አፍ መፍቻ ቋንቋ ........ 10
2.5.3 የማስረፅ የስህተት ምንጭ ........ 11
2.5.4 ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ........ 11
2.5.5 ድምጽ ልሳናት ........ 12
2.6. ስህተትን የመለየት ዘዴ ........ 12
2.6.1 በአረፍተነገር ቅርፅ ላይ መሰረት ያደረገ የስህተት ትንተና ክፍፍል ........ 13

2.6.2 ስነ ልሳናዊ ክፍፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ..... 13
2.6.3 ተግባቦታዊ ተፅእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት ክፍፍል ..... 13
2.6.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... 14
ምዕራፍ ሶስት ..... 16
የአጠናን ዘዴ ..... 16
3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ..... 16
3.2 የመምህራን የናሙና አመራረጥ ..... 16
3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ..... 16
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..... 17
3.4.1. የተማሪዎች ድርሰት ..... 17
3.4.2 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ..... 18
3.4.3. የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ ..... 18
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 19
ምዕራፍ አራት ..... 20
የመረጃ ትንትና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..... 20
4.1. በድርስቶቹ ውስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተቶች ብዛት ..... 20
4.2. አበይት የስህተት ዓይነት ምድቦች ..... 22
4.2.1. የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ..... 24
4.2.1.1. የሆሄያት ቅርፅ ..... 25
4.2.1.2. ግድፈት ..... 26
4.2.1.3 የቃላት ድግግሞሽ /ድርታ/ ..... 27
4.2.1.4. የሆሄያት ጭመራ /እከላ/ ..... 28
4.2. 2. የቋንቋ አወቃቀር ..... 29
4.2.2.1. የቃላት አጠቃቀም ..... 30
4.2.2.2. የአረፍተነገር ስምምነት ስህተት ..... 31
4.2.2.3. የመስተዋድድ ስህተት ..... 31
4.2.2.4. የጾታ፣ የመደብና የቁጥር ስምምነት ..... 32
4.2.3. የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ..... 33
4.2.3.1. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ..... 34

4.2.3.2. የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ........ 35
4.2.3.3. የድርብ ሰረዝ አጠቃቀም ........ 36
4.2.3.4. ቅንፍ ........ 37
4.2.3.5. አንድ ነጥብ (ይዘት)........ 37
4.2.4. መለየት ያልተቻሉ የስህተት ዓይነቶች ........ 38
4.3. የስህተት ምንጭ ........ 39
4.3.1. ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ........ 40
4.3.2. አፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ........ 43
4.3.3 የማስረፅ ስልት ........ 44
4.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ........ 49
4.3.5. ድምጸ ልሳናት ........ 50
4.4. የውጤት ማብራሪያ ........ 53
ምዕራፍ አምስት ........ 58
ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሐሳቦች ........ 58
5.1 ማጠቃለያ ........ 58
5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 61
ዋቢ ጽሑፎች ........ 62
አባሪዎች ........ 65
አባሪ ሀ፡- ለተማሪዎች የቀረበ የጹሁፍ መጠይቅ ........ 65
አባሪ ለ፡- ለመምህራን የቀረበ የፁሁፍ መጠይቅ ........ 74
አባሪ ሐ ፡ ለተማሪዎች የቀረበ የድርሰት መልመጃ ........ 84
አባሪ መ፡- ለቋንቋ አጠቃቀም የቀረበ የስህተት ምሳሌ ........ 86
አባሪ ሠ፡ ለቋንቋ አወቃቀር የቀረበ የሥህተት ምሳሌ ........ 87
አባሪ ረ፡- ለስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ቀረበ የስህተት ምሳሌ ........ 88
አባሪ ሰ፡- መለየት ያልተቻሉ የስህተት ምሳሌ ........ 89

# የሰኝጠረዥ ማውጫ

**ሰንጠረዥ** **ገጽ**


ሰንጠረዥ 1፡- በድርሰቶቹ ውስጥ የተገኙት ስህተቶች ከነዝርዝር መረጃቸው ........................ 21

ሰንጠረዥ 2- ተጠኚ ተማሪዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ እንደ ስህተት ዓይነታቸው በየምድቡ የተፈፀሙ ስህተቶች ዝርዝር መረጃ፡፡ ........................................... 22

ሰንጠረዥ 3፡- በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፅሙ የስህተት ዓይነቶች ዝርዝር መረጃ ........................................................................... 25

ሰንጠረዥ 4፡- በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መረጃ ........................................................................... 30

ሰንጠረዥ 5፡- በሰርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መረጃ ........................................................................... 34

ሰንጠረዥ 6፡- መለየት ያልተቻሉ የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶች ................... 38

ሰንጠረዥ 7፡- መልመጃዎችን በሚመለከት ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ፡፡ ..... 44

ሰንጠረዥ 8፡- መልመጃዎችን በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ፡፡ ..... 45

ሰንጠረዥ 9፡- በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎችን የሚመለከት የመምህራን መጠይቅ ምላሽ፡፡ ........................................................................... 47

ሰንጠረዥ 10፡- በመማሪ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎችን የሚመለከት የተማሪዎችና የመምህራን መጠይቅ ምላሽ ........................................................... 48

ሰንጠረዥ 11፡- ድምፅ ልሳናትን በሚመለከት ከተማሪዎቹ ፅሁፍአዊ መጠየቅ የተገኝ ምላሽ . 50

ሰንጠረዥ 12፡- ድምጸ ልሳናትን በሚመለከት ከመምህራን ፅሁፋዊ መጠየቅ የተገኘ ምላሽ .... 51

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ዓለም አሁን በደረሰበት የስልጣኔ ደረጃ ሰዎች በቴሌቪዥን በኢንተርኔት እና በሳተላይት መልእክት ማስተላፍና መቀበል ችለዋል፡፡ ሰው በእነዚህ በረቀቁ የመገናኛ ዘዴዎች መጠቀም ከቻለ የፅህፈት ትምህርት ለምን ያስፈልጋል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህን በተመለከተ ሰሎሞን ዮሀንስ እና ሌሎች (1994፡138) Troyib (1990፡2) ጠቅሰው ሰው በፅህፈት በኩል ይማራል፣ ያስባል፣ እውቀቱንም የግል ገንዘቡ ማድረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በፅህፈት አዲስ ሃሳብን የማመንጨት ዘዴ በመሆኑ ሀሳቡን በሚታይ እና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላፍ ያስችለዋል፡፡ ጽህፈት ምሁራን እውቀታቸውን የሚያንጸባርቁበት በማህበራዊ ህይዎታቸው ውስጥ ማስታወሻ በመያዝ፣ ደብዳቤ እና ሪፖርቶችን ለመፃፍም ሆነ ለማቅረብ የሚችሉበት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

ከላይ በምሁራኑ የተገለፀው ሃሳብ የፅህፈትን ፋይዳ አጉልቶ የሚያሳይ ቢሆንም ማንኛውም ድርሰት በተሟላ እና በተዋጣ ሁኔታ ይጻፍ ዘንድ ፅሁፋዊ /ድርሰታዊ/ ደንቦችን/ህጎችን/ መገንዘብ ተገቢ እንደሆነና እነዚህም ህጎች ከፊደል ጠቀስ ደንቦች እና ይዘት ነክ ጉዳዮች አኳያ ሊታዩ እንደሚችሉ የሻው (1996፡219) ገልጸዋል፡፡

ድርሰት የሚፅፍ ሰው የሚፅፍበትን ቋንቋ ሆሄያት ቅርፅና መልክ ከነተወላጆቻቸው ማወቅ፡፡ ለምሳሌ በአማርኛ የሚጽፍ ሰው ከሀ-ፐ ያሉትን ሆሄያት መለየት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ስለ ቃላት ምርጫ፣ ስለ አረፍተነገር አመሰራረት፣ ስለ ስርአተ ነጥብ አጠቃቀምማወቅ ግድ ነው፡፡ አንድ ፀሀፊ በተሳካ ሁኔታ ድርሰት መፃፍ ይችል ዘንድ ከላይ በየሻው የተጠቀሱትን ደንቦች/ ህጎች/ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ፣ልምምድ ማድረግ እና እራሱን ማሻሻል ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Ariningsih (2010) ተማሪዎች ፅህፈትን ሲማሩ የቋንቋ አጠቃቀም እና የአፃፃፍ ስርአትን በተግባር መለማመድ ይኖርባቸዋል ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ፅህፈት ከንግግር ይበልጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ኢ-አፍፈት ቋንቋ ተናጋሪዎች ድርሰት

በሚፅፉበት ጊዜ በርካታ ስህተቶች ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ስህተቶች በቋንቋ አጠቃቀም ደረጃ ለምሳሌ የሆሄት ግድፈት፣ ጭመራ፣ድረታ የቃላት አጠቃቀም ወዘተ፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እና በአረፍተነገር ስምምነት ችግር በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች ናቸው፡፡

ዋናው ጉዳይ ግን ስህተቶች ተፈጠሩ ሳይሆን እንዴት እና በምን ሁኔታ ተፈጠሩ? እንዴትስ ስህተቶችን ማረም እና ማስወገድ ይቻላል? የስህተቶቹ ምንጮች ሊሆኑ የሚችሉትስ ምንምን ናቸው? የሚሉትን አንኳር ጥያቄዎች መመለስ የስህተቱን ምንጭ ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ባይቻልም እንኳ ለመቀነስ ይረዳል በማለት Richards (1974) ገልጸዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ይህን ጥናት እንዲያጠና ያነሳሳው ምክንያት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተለይ የፅሁፍ ክሂልን ሲያስተምር የተለያዩ ተግዳሮቶች ገጥመውታል፡፡ ተማሪዎች ደብዳቤ ሲጽፉ፣ ማስታወሻ ሲይዙ እንዲሁም ማመልከቻ እና ድርሰት በተጨማሪም መሰል መልመጃዎችን እንዲጽፉ ሲደረጉ ሃሳባቸውን ከራሳቸው አፍልቀው የመፃፍ ችሎታም ሆነ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን በመገንዘቡ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች እንዲጽፉ የታዘዙትን ከተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሄት እና ጋዜጦች ገልብጠው ወይም ሌሎች ሰዎችን አጽፈው የሚመጡ መሆኑንም ጭምር ስለተረዳ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እራሳቸው ተማሪዎቹ የጻፏቸው ከሆኑ የሆሄያት ቅርፅ፣ ግድፈትና ጭመራ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የአረፍተነገር አመሰራረት እንዲሁም ስርአተነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው ያለማስቀመጥ ስህተቶች በማየቱ ነው፡፡

አጥኚው ይህን መሰረት በማድረግ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ፅሁፍ ሲፅፉ ለምን ስህተት ይፈጥራሉ? የስህተቱ አይነት እና ምንጭ ምንድን ነው? የተፈፀሙ ስህተቶች እንዴት ሊታረሙ እና ሊወገዱ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ በአእምሮው ውስጥ ስላጫረበት ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ ከፅሁፎቻቸው ውስጥ ስህተቶችን እና የስህተት ምንጮችን ነቅሶ በማውጣት የስህተት ትንተና ዜደን ተጠቅሞ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ነው፡፡

ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም:-

1. አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶች ለይቶ ማውጣት፡፡
2. ተማሪዎቹ በፃፉዋቸው በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ ያሉትን የስህተት መጠን እና በተደጋጋሚ የተፃፉ ስህተቶችን መዳሰስ፡፡
3. ለስህተቱ መከሰት መንስዔ የሚሆኑ ነገሮችን መለየት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ተጠናቆ ካለቀ በኋላ ለተለያዩ አካላት ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ይገመታል፡፡በዚህ መሰረት:-

- ✓ በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶች፣ መንስኤዎች እና የስህተቶችን መጠን መምህራን እንዲለዩ ያደርጋቸዋል፡፡
- ✓ መምህራን በተማሪዎቹ የተፈፀሙትን ስህተቶች ከለዩ በኋላ ችግሩን በመረዳት ስህተቶቹን ለማረም ይረዳቸዋል፡፡
- ✓ በተለያዩ ተግባራት ላይ የተሰማሩ የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎቹ የፈጸሟቸውን ስህተቶች መነሻ በመድረግ ነባሩን መርሃ ትምህርት፣ የማስተማሪያ መጻሕፍት እና ሌሎች ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እንዲገመግሙ በማድረግ እና ክፍተቱን በመሙላት አዲስ ለሚዘጋጀው ተገቢ የሆኑ ግብአቶችን አሟልተው እንዲያቀርቡ ያግዛቸዋል፡፡

- ✓ ተማሪዎች ጽህፈትን ሲማሩ (ሲለማመዱ) ስህተት እንዴት ሊፈፅሙ እንደቻሉ፣ የስህተታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ፣ በምን መልኩ ማስተካከል እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

በአፋር ክልል በዞን አንድ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በጥናቱ ዋና ትኩረት በተሰጣቸው ዱብቲና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሙትን ስህተቶች እና የስተት ምንጮች መተንተን ላይ ያተኮረ ነው።የተማሪዎችን ስህተት በመተንተን ሂደት፣ በቋንቋ አጠቃቀም፣ በቋንቋ አወቃቀር እና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ትክክለኛነትን የሚመረምር ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ስህተቶች የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች አይደሉም፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ሲጠና የተወሰነ ችግር አጋጥሞት ነበር፡፡ ከችግሮች መካከልም ተጠኚ ተማሪዎች በቀጠሮው ሰዓት አለመገኘት እንዲሁም አንዳንዶቹ ተማሪዎች ደግሞ ፈቃደኛ አለመሆን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው እነዚህን ችግሮች በመታገስና በማግባባት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላት ስያሜዎች

ከዚህ በታች በጥናቱ ውስጥ የሚገኙ የቃላትና የሐረጋት ፍችዎች ቀርበዋል፡፡

- **ድርሰት** (Composition):- አንድ ውስን ርዕሰ ጉዳይን ብቻ መሠረት አድርጎ የሚጻፍ፤ እንዲሁም የአንድን ሀሳብ መልዕክት (ሀሳብ፣ ስሜትና ፍላጎት) ማስተላለፊያ መሳሪያ ነው (የሻው 1996፣220)፡፡
- **የስህተት ትንተና፡-** ስህተቶችን ለመለየትና ለመግለጽ በሂደት የሚታወቅ የምርምር መሳሪያ ነው (Vanpatten. B & Benati. A.G. 2010,82)፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናትና የቀደምት ጥናቶች ግኝት

## 2.1. የድርሰት ምንነት

ድርሰት (Composition) አንድ ውስን ርዕሰ ጉዳይን ብቻ መሠረት አድርጎ የሚጻፍ እነዲሁም የአንድን ሀሳብ መልዕክት (ሃሳብ፣ ስሜት እና ፍላጎት) ማስተላለፊያ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ድርሰት የጽሑፍ ተግባቦት ሕጎችን ስራ በመሆኑ ስርሰት የሚጽፍ ሰው የሚጽፍበትን ቋንቋ፣ ሆሂያት፣ ቅርጽና መልክ ከነዝርያቸው በተጨማሪም የቃላት ምርጫና አመሰራረት ስልትን መገንዘብ ተገቢ ነው (የሻው 1996፣220)፡፡

## 2.2. የስህተት ምንነት

የሰው ልጅ በማህበራዊ ሕይወቱ በሚያደርገው ተራክቦ ያልተማረው የህብረተሰብ ክፍል በንግግር የተማረው ደግሞ በንግግርና በፅሁፍ ተግባቦት ይፈጥራል። ሰዎች በንግግራቸውም ሆነ በፅሁፋቸው አማካኝነት በሚያደርጉት ተግባቦት ፍፁም ስላልሆኑ ስህተቶች ይፈጽማሉ። ዋናው ቁም ነገር ግን ስህተት መፈፀሙ ሳይሆን ከስህተት መማር መቻሉ ነው።

ተማሪዎችም የዚሁ ህብረተሰብ አባል በመሆናቸው በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ስህተት ይፈፅማሉ። ስህተት መፈፀሙ ግን እንደምቹ አጋጣሚ በመውሰድ ከስህተቶች በመማር ቋንቋን መልመድ ይቻላል። ሰዎች በተለይ ታዳጊ ህፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በሚያደርጉት ለመዳ ብዙ ስህተቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ህፃን "ልብላ" በማለት ፈንታ "ኢባ" በማለት ለስህተት ይጋለጣል። ይህን የተፈጥረውን ስህተት ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች እንዲሁም የሰፈሩ ነዋሪዎች "ኢባ" ሳይሆን "ልብላ" ነው የሚባለው በማለት አነጋገሩን በማስተካከል እና ስህተቱን እንዲያርም በማድረግ የአፍ መፍቻ ቋንቋውን በተገቢው ሁኔታ ይለምዳል። ፅህፈትንም በተመሳሳይ ሁኔታ ሊማር ይችላል።

በሌላ በኩል በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደትም ስህተቶች ይፈጠራሉ። ስህተቱ የሚፈጠረው ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ንግግርም ሆነ ፅህፈትን ለመልመድ በሚያደርገው እንቅስቃሴ

ነው። ስህተቱም የሚከሰተው ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ስርአት በአግባቡ ካለመረዳቱ የመነጨ ነው።

በዚህ የጥናት ዘርፍ ምርምር ካደረጉ ምሁራን መካከል Nagara (1983፡ 35-36) ስህተቶችን የአጠቃቀም ስህተት (Performance Error) እና የእውቀት ማነስ ስህተት (Copmetance Error) በማለት በሁለት ክፍሎች ከፍለዋቸዋል።

የአፈፃፀም ስህተት ማለት ግድፈት (mestake)ሲሆን ይህም ማዳጥ (laps) የሚባለው ነው። በዚህ ምክንያት በሚታየው ስህተት ውስጥ የሆሄያት እና የቃላት ግድፈት ተገቢ ያልሆኑ ድግግሞሽ የሆሄያት ጭመራ የመሳሰሉ ስህተቶችን ያካትታል። ተማሪው ለዚህ የሚዳርገው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በችኮላ፣ ለነገሮች ትኩረት አለመስጠት፣ ባልተረጋጋ ስሜት፣ በድካም ውስጥ ሆኖ በሚናገርበት ወይም በሚፅፍበት ወቅት የሚፈጠር ነው። በመሆኑም እነዚህን ግድፈቶች በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ሊፈፅሟቸው ስለሚችሉ ቋንቋውን ምን ያህል እንዳሻሻሉ ሊገልፅ አይችልም።

በሌላ በኩል James (2013) የብቃት ማነስ ስህተት ተማሪዎች የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች እራሳቸው ካረሙት እና የውጭ እርማት ካላስፈለጋቸው እንደ ስህተት አይቆጠርም። ነገርግን ስህተቶችን ራሳቸው በማረም ፈንታ ሌሎች ሰዎች ግብረ መልስ የሚሰጧቸው እና የሚያስተካክሏቸው ከሆነ እንደ ስህተት ይቆጠራል በማለት ገልፀዋል።

በብቃት ማነስ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች የተማሪውን ስህተት እና የጎደላቸውን ነገር ማሳየት የሚያስችል ሲሆን፣ ስህተትን ለመቀነስ የሚቻለው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትምህርቱን ለማወቅ እና ከስህተታቸው ለመታረም በሚያደርጉት ጥረት ነው።

Eills (2008) ስህተትን ከባድ እና ቀላል ስህተት በማለት በሁለት ክፍል መድበዋቸዋል። ከባድ ስህተት ተማሪዎች ትክክለኛውን ቋንቋ ባለማወቅ በብቃት ማነስ ምክንያት የሚከሰት መሆኑን፤ ቀላል ስህተት ደግሞ ተማሪዎች የቋንቋ እውቀት እያለቸው በሆነ አጋጣሚ መጠቀም ሳይችሉ ሲቀር የሚፈፀም ስህተት መሆኑን ገልፀዋል። ይህ በሁለቱም ምሁራን የተገለፀው ሀሳብ Nagara (1983)ስለ አፈፃፀም ስህተት እና የብቃት ማነስ ስህተት ምንነት ከሰጡት ማብራሪያ ጋር በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ተመሳሳይ ነው።

በአጠቃላይ ስህተት የቋንቋ ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋው ለመናገርም ሆነ ለመፃፍ በቂ ልምምድ ባለማድረጋቸው ምክንያት ለስህተት ተጋላጭ ይሆናሉ። ይህም የተፈፀመው

ስህተት ተማሪው የደረሰበትን የቋንቋ ለመዳ ደረጃን እና የቋንቋ ብቃት የሚያንፀባርቅ እንደሆነ ያመላክታል።

## 2.3. የስህተት ትንተና

የስህተት ትንተና ከመስፋፋቱ በፊት በ1950ዎቹ ውስጥ የተማሪዎችን ስህተቶች በመተንተን እና በማንፀባረቅ በወቅቱ ታዋቂ የነበረው ንፅፅራው ትንተና እንደነበር ምሁራን ይገልፃሉ።

ንፅፅራዊ ትንተና ቋንቋን በማስተማር ሂደት የሚፈጠረው የስህተት ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ አሉታዊ ሽግግር ብቻ እንደሆነ የሚገልፅ የጥናት መስክ ነበር። የንፅፅር ትንተና መላምት አራማጆች ዘንድ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ማነቆ የሆነው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት መሆኑን ጠቁመዋል። ይሁን እንጂ Richard's.&Schmidt (2002) የንፅፅር ትንተና በ1960ዎቹ የዳበረ ቢሆንም ተማሪዎቹ ለፈፀሙት ስህተት ዋነኛው እና ብቸኛው ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለመሆኑ እና ሌሎችም የስህተት ምንጭ መኖራቸውን ሀሳብ አቅርበዋል። በተጨማሪም Hasyim, A (2002) የሁለተኛ ቋንቋን መማር የበለጠ ውስብስብ እንደሆነ ገልፀው ስህተቶች ግን በአፍ መፍቻ ጣልቃ ገብነት ብቻ ሳይሆን በታላሚው ቋንቋ በራሱ ደንቦች (ስርአቶች) የአተገባበር ችግር ሊከሰት እንደሚችል ጠቁመዋል። ስለዚህ የንፅፅር ትንተና ከአፍ መፍቻ ጣልቃ ገብነት ውጪ ሌሎች የስህተት ምንጮችን ማጥናት (መተንተን) ባለመቻሉ ካሳየው ድክመት የተነሳ የስህተት ትንተና ሊመጣ ችሏል።

የስህተት ትንተናን ምንነት በተመለከተ Vanpatten.B & Benati.A.G (2010:82) እንደገለፁት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስህተቶችን ለመለየት፣ ለመግለፅ እና ለማብራራት በሂደት የሚታወቅ የምርምር መሳሪያ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም Gass,s & Selinker,L.(2008:517) ተማሪዎች በሚያደርጉት ስህተት የሚጀመር እና ከዚያም ለማስማማት የሚሞከር የሁለተኛ ቋንቋ መረጃን የመተንተን ሂደት እንደሆነ አብራርተዋል።

በዚህ ጥናት በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈፅሙቸው ስህተቶች፣ የቋንቋ አጠቃቀም ለምሳሌ የሆሄያት ግድፈት ፣ ቅርፅ፣እና

የቃላት አጠቃቀም፣ የቋንቃ አወቃቀር ፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች ተለይተው ተተንትነዋል፣ ማብራሪያም ተሰጥቷቸዋል ፡፡

## 2.4. የስህተት ትንተና ጠቀሜታ

የስህተት ትንተና ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ፅህፈትን ሲማሩ ስህተት ይፈፅማሉ። ስህተትን መሰረት አድርጎ ትንተና ማካሄድ ለተማሪዎች፣ ለመምህራን ለስርአተ ትምህርት አዘጋጆች እና ለተማራማሪዎች ጠቀሜታዎች እንዳሉት ምሁራን ይገልፃሉ።

Richards, J & Schmidt.R. (2010) በበኩላቸው ተማሪዎች ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ የስህተታቸው መንስኤ እና ያጋጠማቸው ችግር ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል።

Weirresh (1991) መምህራን ስህተቶችን በመረዳት ለተማሪዎቹ የሚያስተምሩትን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጡትን መልመጃዎች እና ፈተናዎች በጥንቃቄ አዘጋጅተው ተማሪዎቹ የተሻለ ልምምድ እንዲያደርጉ እንዲሁም ተገቢውን የማስተማሪያ ግብአቶችን እንዲመርጡ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል። በተጨማሪም በዘርፉ ለተሰማሩ የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪው ውጤታማ መሆን ያልቻለበትን ችግር በመረዳት መርሀ ትምህርቱ፣ መፅሀፍትን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ይረዳቸዋል። ለተማሪዎችም በሁለተኛ ቋንቋ ፅህፈትን ሲማሩ የእውቀታቸውን ልኬታ የሚገመግሙበት፣ ስህተት እንዴት ሊፈፅሙ እንደቻሉ፣ በምን አይነት መልኩ ማረም እና ማስተካከል እንዳለባቸው በመገንዘብ ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ ያግዛቸዋል።

በአጠቃላይ የስህተት ትንተና ተማሪዎች ፅህፈትን ሲማሩ የስህተታቸው መንስኤ እና ችግር እንዲሁም ያላቸው የብቃት ደረጃን በመለየት መምህራን፣ የስርአተ ትምህርት አዘጋጆች እና ተመራማሪዎች ችግሩን ተረድተው ሁሉም በየፊናቸው የተሳለጠ ስራ እንዲሰሩ ይጠቅማቸዋል።

## 2.5. የስህተት ምንጮች

በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ የንፅፅር ትንተና አራማጆች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዋናው እና አስቸጋሪው የስህተት ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር መሆኑን ገልፀዋል። ይሁን እንጂ ለስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ አሉታዊ ሽግግር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ያሉ መሆኑ ተገልጿል።

Dulayetal (1982,197) የስህተት አይነቶች ምንጫቸው ይሄ ነው ወይም አንድ ነው ብሎ እያንዳንዱ ስህተት ማስቀመጥ አይቻልም። ስህተት የብዙ ነገሮች ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰዋል። Norish (1993) ስህተቶች ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል በሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ለትምህርቱ ከሚቀርብበት የማስተማሪያ ግብአቶች ምርጫ፣በቋንቋ ትምህርቱ ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎቹ አማካኝነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ተማሪዎቹ የትምህርት መርጃዎችን ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ስህተቶች ሊከሰቱ ይችላሉ በማለት አብራርተዋል።

James (2013:179-200) በበኩላቸው ለተማሪዎች ስህተት መፈፅም የተለያዩ የስህተት መንስኤዎች መኖራቸውን አሳውቀዋል።

### 2.5.1 የውስጥ ቋንቋ ተፅእኖ

ይህ የስህተት ምንጭ በውስጠ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ምክንያት የሚፈፀሙ ስህተት ነው፡፡ ይህም ስህተት መንስኤው የአፍ መፍች ቋንቋ ሳይሆን በታላሚ ቋንቋ በራሱ የሚከሰት ችግር ነው፡፡ ተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋን አድስ ስርአት ከለመዱ በኋላ የታላሚውን ቋንቋ ህጉን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል በመረዳት ለመናገርና ለመፃፍ በሚያደርጉት ሙከራ የሚፈጸም ሰስህተት እንደሆነ James.C. (1998) ገልፃዋል ፡፡

Brown (1994፤214) ታላሚው ቋንቋ የራሱ የሆነ መዋቅራዊ ስርአት ያለው ቢሆንም ለሁሉም ቋንቋዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ሊያገለግል አይችልም ፡፡ ተማሪዎች ግን ይህን መዋቅራዊ ስርአት በአጠቃላይ ለሁሉም ቋንቋ እንደሚሰራ አድርገው ይወስዱታል በማለት ገልጸዋል፡፡ አማረኛን በሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ /መታ/ ብሎ ምታ፤ ሰራ ብሎ /ስራ/ ካለ ጠጣ ብሎ /ጥጣ/፤ ቀማ ብሎ /ቅማ/ እያለ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ቢጠቀም በታላሚው ቋንቋ ውስጣዊ ውስብስብ ባህሪ ተፅኖ የተሳሳተ ማጠቃለያ አማካኝነት የሚፈፀም ስህተት እንደሆነ መግለፅ ይቻላል፡፡

የተሳሳተ ማጠቃለያ ሲባል ተማሪዎች ታላሚውን ቋነቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አድስ ስርአት መሰረት አድርገው በቋንቋ ለመጠቀም ሲሞክሩ የሚሳሳቱትን ማለት ነው ፡፡

Brown (1994፤164) እንደገለፁት ለቋንቋ ስህተት የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ ሳይሆን ያልተሟላ ትምህርት፡ የተሳሳተ ተዛምዶና ቃላትን አላገባብ መጠቀም

ለሚፈፀሙ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው፡፡ Ngara (1983፤37-40) እንደገለፁት ባልተሟላ ትምህርት የሚፈፀም ስህተት ስንል የቋንቋ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር ቃላት፡ የአገላለፅ ስልት ወይም ሌሎች የታላሚውን ቋንቋ ባህሪያት ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል በመማሩ የተነሳ የሚከሰተውን ስህተት ማለታችን ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪው በቋንቋው ውሰጥ የሚገኙትን ሰዋሰዋዊ ስርአቶች በከፊል በስህተት በከፊል ደግሞ ያለስህተት ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ፡፡

Ngara (1983፤2.39) ቃላትን ያለግባብ መጠቀም ሲባል ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ለአድማጩ (ለአንባቢው) ሀሳቡን በታላሚው ቋንቋ ለመግለፅ እረጃጅም ዓረፍተ ነገሮችን ሲጠቀሙ አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ ይስተናገዳሉ፡፡

በአጠቃላይ የውስጥ ቋንቋ ስህትተ የሚያሳየው የቋንቋ ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል በመረዳቱ የተነሳ የሚፈፅማቸው ስህትቶች ናቸው ፡፡ እነዚህም የውስጥ ቋንቋ ስህተቶች በተሳሳተ ማጠቃለያ ፡ የታላሚውን ቋንቋ ያልተሟላ ህግን በመጠቀም ድግግሞሽ ማብዛት ወዘተ የተነሳ ስህተቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ James (2013: 93) ገልፀዋል፡፡

## 2.5.2 አፍ መፍቻ ቋንቋ

በንፅፅራዊ ትንተና ተመራማሪዎች አተያይ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ለስህተት መጋለጥ ዋነኛው መንስኤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ነው የሚል እሳቤ እንደነበር ምሁራን ይገልፃሉ። Richards & Schmidt (2010) ስለ ንፅፅር ትንተና የሰጡትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ዋና ዋና ችግሮች ናቸው ብለው ከፈረጇቸው መካከል አንዱ የተማሪው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ምክንያት የሚከሰት እንደነበር ጠቁመዋል። ይህንን ሀሳብ Browon (1994: 213-214) በፃፉት ፅሁፍም ይጋሩታል።

በመሆኑም ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ከመለማመዳቸው አስቀድሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ሲማሩ በሆሂያት፣በቃላት፣በአረፍተነገር ግንባታ እና በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ስህተት ሊከሰት ይችላል።ይሁን እንጂ የሚከሰቱት ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ ብቻ እንዳልነበር (Corder 1981 & James 2013) አመላክተዋል።

በጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ መገንዘብ እሚቻለው የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ለስህተት መፈጠር ብቸኛው የስህተት መንስኤ እንዳልሆነ እና ሌሎች የስህተት ምንጮች መኖራቸውን ያስረዳል።

### 2.5.3 የማስረፅ የስህተት ምንጭ

ይህ ስህተት መንስኤው በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የሚመለከት ነው።ይህንንም James (2013:) በአራት ንኡሳን ክፍሎች ከፍለዋቸዋል።እነዚህም:— በመማሪያ ቁሳቁስ የሚመነጭ ስህተት፣ በመምህራን የመናገር ስልት የሚመነጭ፣ መልመጃዎችን መሰረት ያደረገ የስህተት ምንጭ እና ከማስተማር ቅደም ተከተል አንፃር የሚመነጭ ስህተቶች ናቸው።

በመማሪያ ቁሳቁሶች የሚመነጭ ስህተት የቋንቋ ትምህርቱን ለማስተማር የቀረቡት የማስተማሪያ መሳሪያዎች የተማሪው መፅሀፍት፣ የመምህሩ መምሪያ፣ መርጃ መሳሪያ እንዲሁም የመማሪያ ክፍል በብቃት እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ አለመዘጋጀታቸው እና አለመደራጀታቸው ለስህተት መንስኤ ይሆናሉ።Broughton etal (1978:134) ከላይ የተዘረዘሩት የመማሪያ ቁሶችን በመጥቀስ መርሀ ትምህርቱ፣መምህራን እና ተማሪዎችንም በመጨመር በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ስህተት እንደሚከሰት ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ አብራርተዋል።መምህራንም የቋንቋውን ትምህርት ለማስረተማር በቅደም ተከተል የተሻሉ ይዘቶችን እና መልመጃዎችን በመምረጥ፣ የማስተማር ስልቶችን ከቀረበው ይዘት ጋር አጣጥመው ካላስተማሩ ትምህርቱ ከታሰበበት ግብ ላይደርስ ይችላል።በመሆኑም መምህሩ ትምህርቱን ለማስተማር የሚጠቀምበት ዘዴ አጥጋቢ አለመሆኑ እንዲሁም ማስተማር የፈለገውን የቋንቋ ይዘት እና መልመጃ ባለመዘጋጀቱ የተነሳ በተገቢው መንገድ መልእክቱን በትክክል ላይናገር ይችላል።በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ትክክለኛውን ሀሳብ ማግኘት ስላልቻሉ ለስህተት ይጋለጣሉ።

### 2.5.4 ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

ይህ የስህተት ምንጭ ቀደም ሲል ከተዘረዘሩት የስህተት ምንጮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም ከተማሪወቹ የግል ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ ነው ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ከመማሪያ ክፍል ውጭ በአካባቢያቸው ስለሚታዩትና ስለሚፈጠሩት መልካም ሆነ መጥፎ ገጠመኝ እንዲሁም ስለራሳቸውና ስለቤተሰባቸው ሁኔታ በአዕምራቸው ውስጥ ይዘውት የመጡትን

ጉዳይ በማሰላሰል በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርት እንደማይከታተሉ ተፅኖ እንደሚያደርግባቸው (ደብሬ 1990 ፡110) ኖሪሽን በመጥቀስ በዚህ አይነት ሁኔታ የሚፈፀሙት ስሕተቶች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ስህተት መፍጠር እንደ አላስፈላጊ ክስተት እና እንደ ነውር የሚታይ ሳይሆን በመማር ማስተማሩ ሂዴት የትምህርቱ አንድ አካል ሊሆን እንደሚችል Richards (1974፡ 23)ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን ተማሪው በሚማርው ቋንቋ አውንታዊ አተያይ እና የመማር ፍላጎት እንድሁም ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሊለው በፅሁፍና በንግግሩ ውስጥ ስተቶች ሊፈፃሙ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.5.5 ድምጽ ልሳናት

የአማርኛ ድምጸልሳናት 33 ይደርሳሉ ፡፡ የመደበኛው ድምጸ ልሳላት ብዛትን በዘርን ሲባዛ (33×7)=231 በተጨማርም38 ዲቃላ ሆህያት በድምሩ 269 ድምጾች ይገኛሉ ;; ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት መከሰት መንስአው የቋንቋው ድምጸ ልሳናጽ ብዛት እንደሆነ ስዩም ከበደ እና ሌሎች ( 1994 ; 132- 133 ) ፤ እንደለ ተስፋየ (1990፡31) አማርኛን የማስተማርያ ስነ ዘደ በሚለው ጸሁፋቸው ዩሀንስ አድማሱ (1966; 109-110) ዋቢ አድርገው ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከሆሂያት ብዛት የተነሳ ቅርጻቸውን በትክክል መለየት ባለመቻላቸው ድርሰት ሲጽፉ ሀሳባቸውን በትክክል ለመግለጽ እንቅፋት ከመሆናቸው ባሻገር ለንበትም አስቸጋሪ ናቸው ፡፡

ለምሳሌ ፤- በኋላ በሚለው ፈንታ በሆላ በማለት ዲቃላ ሆህያትን በሳብእ ቅርጽ የመተካት ሁኔታ ይታያል ፡፡ በዚህም ምክንያት በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ስህተት ይፈጠራል፡፡

## 2.6. ስህተትን የመለየት ዘዴ

ትክክለኛ የሆነ የስህተት ትንተና ዘዴ ማቅረብ እንዳልተቻለ lott (1983:253) ገልፀዋል።ምክንያቱም በትንተናው ዙሪያ በርካታ ስህተቶች በመከሰታቸው የተነሳ ስህተቶችን በአይነት በአይነታቸው ለመመደብ አስቸጋሪ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ጨምር ተናግረዋል።

Dulay et.al. (1983:246-261) በበርካታ ተመራማሪዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የዋሉትን ማለትም በአረፍተነገር ቅርፅ ላይ፣በንፅፅር ትንተና ላይ እና በተግባቦት ላይ መሰረት ያደረገ ክፍፍል በማድረግ ለእያንዳንዱም ማብራሪያ ቀርበዋል።

## 2.6.1 በአረፍተነገር ቅርፅ ላይ መሰረት ያደረገ የስህተት ትንተና ክፍፍል

ተማሪዎች ቋንቋን በፅሁፍ በሚማሩበት ወቅት የሚገነቧቸው አረፍተ ነገሮች ውጫዊ ቅርፅ ሲታይ የተለያዩ ስህተቶች ሊገኙ እንደሚችሉ በመገመት ነው።በመሆኑም ተማሪዎች አረፍተነገር ሲመሰርቱ አላስፈላጊ እና ተገቢነት የሌላቸውን አካላት ሲያካትቱ በዚህ ተቃራኒ ደግሞ አስፈላጊ እና ተገቢነት ያላቸውን የአረፍተነገር አካላት ላያካትቱ ይችላሉ።

በዚህ ምክንያት ስህተቶች የሚመደቡት ተማሪዎች በሚፅፏቸው አረፍተነገሮች ውስጥ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች አጥኚው የሚመድበው ይህንን መነሻ በማድረግ ነው ።

## 2.6.2 ስነ ልሳናዊ ክፍፍሎችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል

ይህ ዘዴ በበርካታ ባለሙያዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ እና በርካታ ጥናቶች የተከናወኑበት የፅህፈት ትንተና ስልት እንደሆነ dulay et.al (1982:150) ገፅፀዋል።ስለሆነም በስህተት ትንተና ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ሲነሳሱ እንደ መነሻ አድርገው የሚጠቀሙበት ስነልሳናዊ ክፍፍሎች ነው።

የስህተት ትንተናውም በድምፅ፣ በምእላድ፣ በቃላት አጠቃቀም እና በስነ አገባብ ላይ ሊያጠና ይችላል ይህ የሚወሰነው የተነሱበት አላማ ነው።በመሆኑም በዚህ የስህተት አከፋፈል ስልት አጥኚው ስህተቶችን በጥንቃቄ ለቅሞ ካደራጀ በኋላ እንደ ስፋታቸው ሁኔታ ተተንትነዋል።

## 2.6.3 ተግባቦታዊ ተፅእኖ መሰረት ያደረገ የስህተት ክፍፍል

የስህተት ትንተና ስልት የሚያነጣጥረው ተግባቦትን የሚያሰናክሉ ስህተቶች ላይ ነው።ይሁን እንጂ ለተግባቦቱ መሰናክል የሆኑት የትኞቹ ስህተት እንደሆኑ ለጥያቄው ምላሽ የሚሰጥ በግልፅ ተብራርቶ የተቀመጠ የስህተት ትንተና ስልት አለመኖሩን dulay et.al (1982:189-190) ጠቅሰዋል። በመሆኑም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በርካታ ስህተቶች የተስተናገዱበት፣ በግልፅ እና በማያወዛግብ ሁኔታ ያልተፃፈ ከሆነ አንባቢው የተፃፈውን ፅሁፍ በአግባቡ አንብቦ ሀሳቡን ካለመረዳቱም በተጨማሪ የተግባቦት

ሂደቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል።ስለዚህ ለተግባቦቱ መሰናክል ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት ችግሮች በየዘርፋቸው ተደራጅተው ተተንትነዋል።

Norrish (1983:81-92) ከዚህ በላይ የተዳሰሱትን የስህተት አከፋፈል ዘዴዎች ቅድመ ግንብዛቤ መሰረት ያደረገ እና የተፈፀሙትን ስህተቶች መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ስልት በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለዋቸዋል።

**ሀ. ቅድመ ግንዛቤ መሰረት ያደረገ የስህተት ክፍፍል**

ይህ ዘዴ ቀዳሚው እንደመሆኑ መጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በድርሰታቸው ውስጥ ይፈፅሟቸዋል ተብለው የሚታሰቡትን ስህተቶች በአይነት በአይነታቸው ቀድሞ በተሰጣቸው ምደባ መሰረት ማስቀመጥ ነው።

**ለ. ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ዘዴ**

ይህ ዘዴ Hudson (1976) በተባለ ምሁር ተግባር ላይ ውሏል፡፡አፈፃፀሙም በቅድሚያ በድርሰቱ ውስጥ የተገኙ ስህተቶችን ሁሉ ለቅሞ በማውጣት በተዘጋጀው ካርድ ላይ ይመዘገባል፡፡ከዚህ በኋላ ተመሰሳይነት ያላቸውን ስህተቶች በመለየት በአንድ ቋት ውስጥ በማስገባት ትንተናው ይካሄዳል፡፡ይህን ለመተግበር ሰፋ ያለ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ እንደ ደካማ ጎን የሚያስቀጥረው መሆኑን Norrish (1993፡83-86) ገልፀዋል፡፡

## 2.6.4 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ተተኳሪነት በሚመለከት የተደረጉ ጥናቶች ይዳሰሳሉ፡፡ እነዚህም ጥናቶች ለሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች ናቸው፡፡በዚህም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉትን እናያለን፡፡ እነዚህም፡-

ደብሬ (1990) በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና የሚል ርዕስ ያለው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የደበሬ ተሰማ የጥናት ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ በመመርመር የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶችና ምንጮችን ለመለየትና ለስህተቶቹ መቃለልም የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡ በተጨሪም ይህ ጥናት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

በጥናቱ ውጤትም የስህተት አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም እና አወቃቀር፣የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እንዲሁም ስህተቶችን ለመለየት አስቸጋሪ የሆኑ ነጥቦች መኖራቸውን ጠቁመዋል።ለስህተቱ መከሰት መንስኤ ያደረጉትም በአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ በውስጥ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደት፣ ስነልቦናዊ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተፅእኖዎች የተፈፀሙ መሆናቸውን በጥናታቸው ገልፀዋል።

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ልዑልሰገድ አሰፋ (1997) በወላይተኛ እና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችና የሰህተቶች ምንጭ ትንተና የሚል ርዕስ ያለው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በአዋሳ ከተማ በሚገኙ ሁለት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ በ10 +1 /ሰርትፍኬት/ መርሃ ግብር በመማር ላይ ያሉ እፋቸውን በወይላተኛና ሲዳምኛ ቋንቋዎች የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅማቸውን ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች መለየት ነው፡፡ትኩረት ያደረጉትም ስነልሳናዊ ስህተቶች ላይ ነው። ይህንንም በድምፅ፣ በቃላት በሀረግ እና በአረፍተነገር ደረጃ የተፈፀመ ስህተት በማለት በአራት ክፍሎች ከፋፍለው አቅርበዋል።ለስህተቱ መከሰት በምክንያትነት ያቀረቡት የአፍ መፍቻ ተፅእኖ፣ የውስጥ ቋንቋ ተፅእኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ድክመት እንዲሁም ስነልቦናዊ ሁኔታዎች ናቸው።በተጨማሪም ይህ ጥናት በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ላይ ያነጣጥራል፡፡

በሁለቱ ተመራማሪዎች የጥናት ውጤት መሰረት የተጠቀሱት የስህተት ምንጮች ለተጠኚ ተማሪዎች የፅሁፍ ስህተት መንስኤ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገጿል።

ይህ ጥናት ከደብሬ ተሰማ (1990) እና ከልዑልሰገድ አሰፋ (1997) የሚያመሳስለው በሁለተኛ ቋንቋ ላይ የስህተት ትንተና ማድረጉ ነው። እነሱ የተጠቀመበት የመርጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መጠይቆች እና የተማሪዎች ድርሰት መሆኑ በተጨማሪም በስህተት ምንጭነት እነሱ ከጠቀሱት አራት ነጥቦች መካከል የአፍ መፍቻ እና የውስጥ ቋንቋ ተፅእኖ በሚለው ሀሳብ ላይ ይመሳሰላል፡፡

ይሁንእንጅ ይህ ጥናት ከደብሬ እና ልዑልሰገድ ጥናት የሚለየው የቋንቋ ድምፀ ልሳናት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ጥናት ማድረጉ፣ በአይነታዊ እና በመጠናዊ የአተናተን ዘዴ መጠቀሙ፣ በተጠኚ ተማሪዎች ብዛት፣ የጥናቱ ቦታ እና በመምህራን ናሙና አመራረጥ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በአፋር ክልል በዞን አንድ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ነው።እነዚህም ዱብቲ እና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው።አጥኚው ይህን ጥናት ለማካሄድ የተጠቀመበት ዘዴ ከወሳኝ ንሞና (Non probability sampling) መካከል አመቺ ንሞና (convence sampling) በመጠቀም ነው።

አጥኚው ካለው የቦታ ርቀት፣ የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም መደበኛ ስራው ላይ እንቅፋት እንዳይፈጥር በማሰብ በቅርበት ያገኛቸውን ትምህርት ቤቶች ለመምረጥ ችሏል።

## 3.2 የመምህራን የናሙና አመራረጥ

አጥኚው ለዚህ ጥናት ይበጀኛል ያለውን ከወሳኝ ንሞና ዘዴዎች መካከል ጠቅላይ ንሞናን በመጠቀም በዱብቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት እና በሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ የሚያስተምሩትን ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቷል። ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያካተተበት ምክንያት ቁጥራቸው አናሳ በመሆኑ ነው።

## 3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በአፋርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረ ነው።አጥኚው ለዚህ ጥናት የተጠቀመበት እድል ሰጪ የንሞና አመራረጥ ዘዴ መካከል ቀላል የእጣ ንሞና (simple randum sampling) ነው።

በዚህ መሰረት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በ12ኛ ክፍል በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ብዛት 220 መሆናቸውን ካወቀ በኋላ ከነዚህ መካከል 50% (ሀምሳ በመቶ) የሚሆኑትን 110ተማሪዎች ለጥናቱ ቀርበዋል።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናታዊ ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቆች እና በተማሪዎች የተፃፉ የተለያዩ የድርሰት መልመጃዎች ናቸው።

### 3.4.1. የተማሪዎች ድርሰት

ተማሪዎች ድርሰት የሚፅፉት በሁለተኛ ቋንቋቸው እንደመሆኑ መጠን የነሱን የትምህርት ደረጃ፣ በቋንቋው ላይ ያላቸው ችሎታ፣ ከባህላቸው እና ከማህበራዊ ህይወታቸው ጋር የተገናኙ ድርሰቶችን እንዲፅፉ ማድረግ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት የሚሰጠው ፋይዳ የላቀ ነው። በመሆኑም ለዚህ ጥናት የሚውሉ በአጥኚው የተዘጋጁ አስር ርእሶች ተዘጋጅተው ቀርበዋል። ከነዚህ ከተሰጡት ርዕሶች መካከል በተሻለ ሁኔታ ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚያስችላቸውን እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ርእሶችን መርጠው በሁለት ዙር በክፍል ውስጥ እንዲፅፉ ተደርጓል።

በመጀመሪያው ዙር የተሳታፊ ተማሪዎች ብዛት 110 ናቸው ።በሁለተኛው ርእስ ላይም በተመሳሳይ መልኩ ተፈፅሟል።ድርሰቱንም ሲፅፉ ሰፋ ያለ ጊዜ በመስጠት ሳይፈሩ እና ሳይጨነቁ እንዲፅፉ ከማድረግ ባሻገር በፅሁፋቸው ውስጥ ያሉ ስህተቶችን ከእውቀት ማነስ ብቻ የመጣ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ያግዛል ተብሎ ስለተገመተ ነው።ተማሪዎች ድርሰቱን በክፍል ውስጥ ብቻ እንዲፅፉ የተደረገበት ምክንያት በቤት ስራ መልክ ከተሰጣቸው ሌሎች ከነሱ ችሎታ በላይ እውቀት ያላቸው ሰዎች ስለሚያሰሩ ነው። ርእሶችም በሶስት ቅጂ ተባዝተው የመጀመሪያና ሁለተኛ ድግሪ ባላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንደገመገሙና ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል።

መምህራንም ስህተቶችን በሆሄያት ቅርፅ ድግግሞሽ፣ እከላ (ጭመራ)፣ ግድፈት እንዲሁም በቃላት አጠቃቀም፣ በአረፍተነገር አመሰራረት እና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም አንፃር ያገኛቸውን ስህተቶች ብዛት እና አይነት በአጥኚው በተዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት ሞልተዋል።እነዚህም የምድብ መስፈርቶች የሚዘጋጁት አጥኚው አስቀድሞ ድርሰቶችን በማረም ካገኛቸው ስህተቶች በመነሳት ለዚህ ጥናት አመቺ በሆነ መልኩ ተደራጅተው ተተንትነዋል።

ጥናቱ ስራ ላይ የዋለው ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ ነው። በዚህ መሰረት የተማሪዎችን ስህተቶች መመደብ ተችሏል። ይህ ዘዴ የተመደበበት ምክንያት ስህተቶችን አከፋፍሎ ለመደልደል አመቺ በመሆኑ ነው።

### 3.4.2 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ በጥናቱ መጨረሻ በሚገኘው ውጤት ላይ ተአማኒነት የሌለው ሁኔታ እንዳይከሰት በድርሰቱ መልመጃ ይገኛል ተብሎ ለታሰበው ውጤት የማጠናከሪያ ሀሳብ ለማግኘት ነው።

በተማሪዎች የሚሞላው መጠይቅም አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነርሱም በክፍል አንድ አጠቃላይ የተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ የተዘጋጀ ጥያቄ ነው።ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በምርጫ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የሚይዝ ሲሆን ሶስተኛው ክፍል በ4 የስኬል ደረጃዎች በመከፋፈል የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይዟል።አራተኛው እና የመጨረሻው ደረጃ በፅሁፍ የሚመለሱ ክፍት ጥያቄዎችን ያካተተ ነው።

ለተማሪዎች የሚቀርበው መጠይቅ በሶስት ቅጂ ከተዘጋጀ በኋላ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲገመግሙት ተደርጓል።በግምገማው መሰረት በጥያቄው ውስጥ ግልፅ ያልሆኑ እና አወዛጋቢ ጥያቄዎች ካሉ በመምህራን አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ ስምምነት ላይ ከተደረሰ እንደገና ተሻሽሎ በተጠኚዎች ልክ ተባዝቷል።ተማሪዎቹም መጠይቁ ከመሙላታቸው በፊት ስለ አሞላሉ እና ግልፅ ያልሆነ ጥያቄ ካለ በጥናቱ አቅራቢ ማብራሪያ ተደርጓል።

### 3.4.3. የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዋናው ጉዳይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመዳሰስ ለተመረጠው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው።መጠይቁም አራት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን እነሱም፡- ክፍል አንድ አጠቃላይ የመምህራን መረጃ በተመለከተ የቀረበ መጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በምርጫ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይዟል።በክፍል ሶስት በአራት የእስኬል ደረጃዎች በመከፋፈል የሚመለሱ ጥያቄዎችን ሲይዝ በአራተኛው እና በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በፅሁፍ የሚመለሱ ክፍት ጥያቄዎችን አካቶ ይዟል።

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉት ድረሰቶች፣ የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን እና በተማሪዎች የተሞሉት የጽሑፍ መጠይቆች ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ናቸው ተብለው የታሰቡ ነገሮችን ይጠቁማሉ፡፡ መረጃዎቹ በአይነታዊና መጠናዊ የአተናተን ዘዴ በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንትና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአፍርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ ከጽህፎቻቸው ውስጥ ስህተቶችንና የስህተት ምንጮችን ነቅሶ በማውጣት የስህተት ትንተናን ዘዴ ተጠቅሞ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ነው፡፡

በዚህ መሰረት በምዕራፍ አንድ የተገለፁትን የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ሊመልሱ የሚችሉ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች በዚህ ምዕራፍ ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ፡-

1. የአማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?

2. የስህተቶቹ የድግግሞሽ መጠንስ ምን ያህል ነው?

3. ለስህተቶቹ መከሰት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉት የስህተት ምንጮች እነማን ናቸው?

ከነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች በመነሳት ምላሽ ለመስጠት ተጠኝ ተማሪዎች የጻፉአቸውን ድርሰቶች ፣ከተማሪዎችና ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቆች የተገኙት መረጃዎች ተሰብስበውና በአይነታቸው ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠኝ ተማሪዎች በፀፉአቸው ድርሰቶች መሰረት የድርሰቶቹ ብዛት ፣የተጻፉበት የቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛት፣ አማካይ ስህተት እና የስህተት ድግግሞሽ ለስህተት መገኘት መንስኤ የሆኑትን ውስጠ ቋንቋ ተፅእኖ ፣የእፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ፣የማስረፅ ስልት ተፅእኖ ፣ ስነልቦናዊ ሁኔታውችና ድምጸ ልሳናት ተተንትነው ማብራሪያም ተሰጥቷል፡፡

## 4.1. በድርስቶቹ ውስጥ የታዩ አጠቃላይ የስህተቶች ብዛት

በዚህ ንዑስ ክፍል በድርስት ውስጥ የተገኙት ስህተቶች ከነዝርዝር መረጃቸው የቀረቡበት ነው፡፡ ተጠኚ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት መሰረት የድርሰት ብዛት፣ ድርስቶቹ የተፃፉበት የቃላት ብዛት ፣የስህተት ድግግሞሽ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### ሰንጠረዥ 1፡- በድርሰቶቹ ውስጥ የተገኙት ስህተቶች ከነዝርዝር መረጃቸው

| የድርስት ዓይነት | የድርስቶች ብዛት | ድርስቶቹ የተጻፉበት ቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት | | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ብዛት/መጠን በቁጥር | በመቶኛ | | |
| ድርሰት አንድ | 110 | 8745 | 79.5 | 1821 | 51.64 | 16.55 | 20.81 |
| ድርሰት ሁለት | 110 | 8892 | 80.84 | 1705 | 48.36 | 15.5 | 19.2 |
| ድርሰት አንድና ሁለት | 220 | 17637 | 80.17 | 3526 | 100 | 16.02 | 19.98 |

ከሰንጠረዥ 1 መረዳት እንደተቻለው የስህተት መረጃዎቹ የተቆጠሩት በድርሰት አንድ እና ሁለት መልመጃዎች በተጻፉት 220 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ እነዚህም ድርሰቶች የተጻፉበት የቃላት ብዛት 17637 ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ የተቆጠሩትም ስህተቶች ብዛት 3526 ነው ፡፡ እነዚህ የስህተቶች ብዛት በመቶኛ ሲቀመጡ የስህተቶቹን ብዛት(መጠን) ለጠቅላላው የስህተቶች ብዛት በማካፈል የተገኘውን ውጤት በመቶ በማባዛት የስህተቶቹን መጠን በመቶኛ ማገኘት ተችሏል፡፡

ድርሰቶቹ በሁለት ዙር የተፃፉበት የቃላት ብዛት 17637ሲሆን አንድ ድርሰትም በአማካይ የተጻፈበት የቃላት ብዛት ለማወቅ ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ተገኙትን የቃላት ብዛት ለጻፈአቸው ድርሰቶች ቁጥር በማካፈል ውጠየቱን ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሰረት አንድ ድረሰት በአማካይ 80.17 ቃላት ተጽፎ ይገኛል፡፡ በአንድ ድረሰት ውስጥ የተገኙትን አማካይ ስህተትም ለማገኘት አማካይ የስህተት ብዛት(መጠን) ለተጠኝ ተማሪዎች ለጻፉት አጠቃላይ ድርሰት በማከፈል 16.02 ሲሆን በ80.17 ቃላት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ ለማወቅ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈል የተገኘው ውጤት በመቶ ተባዝቶ 19.98 እነደሆነ መከረጃው ያሳያል፡፡

ድርሰቶቹም የተፃፉበት የቃላት ብዛት 17637 ሲሆን አንድ ድርሰትም በአማካይ 80.17 ቃላት ተፅፈው ይገኛሉ፡፡ በሁለት ዙር በተከታታይ ከተፃፉት 220 ድርሰቶች ውስጥ የተቁጠሩት ስህተቶች ብዛት 3526 ሆኗል፡፡ በአንድ ድርስት ውስጥ የተገኙት አማካይ

ስህተትም 16.03 ነው፡፡ በመቶ ቃላት የተፃፈ አንድ ድርሰት በውስጡ ያለው የስህተት ድግግሞሽ መጠን 19.99 እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

## 4.2. አበይት የስህተት ዓይነት ምድቦች

ቀደም ሲል በክፍል ሶስት የስህተት አተናተን ዘዴ ላይ እንደተገለጸው ስህተቶች በአይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምደባ የስህተት ዓይነት ምድቦች መሰረት ነው፡፡

በዚህ ክፍል ደግሞ በብዛት የታዩት አበይት የስህተት ዓይነቶች፡-

1. የቋንቋ አጠቃቀም
2. የቋንቋ አወቃቀር
3. የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም
4. መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው፡፡

በነዚህ የስህተት ዓይነት ምድቦች ውስጥ የተገኘውን የስህተት መጠን ዝርዝር መረጃ እንደሚከተ

ለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2- ተጠኚ ተማሪዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ እንደ ስህተት ዓይነታቸው በየምድቡ የተፈፀሙ ስህተቶች ዝርዝር መረጃ፡፡**

| የስህተት ዓይነት ምድቦች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ |
| | ብዛት | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | |
| የቋንቋ አጠቃቀም | 928 | 50.96 | 8.44 | 10.61 | 875 | 51.32 | 7.95 | 10 | 1803 | 51.13 | 8.20 | 10.23 |
| የቋንቋ አወቃቀር | 302 | 16.58 | 2.75 | 3.46 | 275 | 16.13 | 2.5 | 3.14 | 577 | 16.36 | 2.62 | 3.27 |
| ስርዓት ነጥቦች | 529 | 29.05 | 4.80 | 6.04 | 505 | 29.62 | 4.59 | 5.8 | 1034 | 29.33 | 4.7 | 5.86 |
| መለየት ያልተቻሉ | 62 | 3.40 | 0.56 | 0.70 | 50 | 2.93 | 0.45 | 0.57 | 112 | 3.18 | 0.51 | 0.64 |
| ድምር | 1821 | 100 | 16.55 | 20.81 | 1705 | 100 | 15.5 | 19.50 | 3526 | 100 | 16.03 | 20 |

ሰንጠረዥ 2. እንደሚያሳየው በሁለቱም ድርሰቶች ከተመደቡት የስህተት ዓይነቶች መካከል ብዙ ስህተት የተቆጠረው በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ ነው፡፡ ተጠኝ ተማሪዎች በሁለት ተከታታይ ዙር በጻፈአቸው 220 ድርሰቶች ውስጥ 3526 ስህተቶች የተገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1803 የሚሆኑት የተገኙት በዚህ ምድብ ውስጥ ነው፡፡ ይህም የስህተት ብዛት (መጠን) በመቶኛ ሲሰላ የስህተቶቹን ብዛት (መጠን) ለጠቅላላው የስህተቶች ብዛት በማካፈል የተገኘውን ውጤት በመቶ በማባዛት የስህተቶቹን መጠን በመቶኛ ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ምድብ ውስጥ የተገኘው የስህተት መጠን በመቶኛ ሰ,ሲሰላ 51.13% ደርሷል፡፡ በአንድ ድርሰት ውስጥ የተገኘው አማካይ ስህተት ለማወቅ አማካይ የስህተት ብዛት (መጠን) ተጠኝ ተማሪዎች ለጻፉት አጠቃላይ ድርሰት በማካፈል 8.20 ሲሆን በአንድ መቶ ቃላት በሚይዝ አንድ ድርሰት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈል የተገኘውን ውጤት በመቶ ተባዝቶ 10.23 እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም በተመለከተ ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ብዙ ስህተት የተገኝበት ምደብ ነው፡፡ ይህም ስህተትተኘኝ ተማሪዎች ከጻፉአቸው ድርሰቶች ውስጥ ከተገኙት 3526 ስህተቶች መካከል 1034 ስህተቶች የተቆጠሩት በዚህ ምድብ ነው፡፡ ከላይ በተገለጸው ቋንቋ አጠቃቀም በተጻፈው ቀመር መሰረት የስህተት ብዛቱ በመቶኛ ሲቀመጥ 29.33% ሲሆን አማካይ ስህተት መጠኑ 4.7 ነው፡፡ አማካይ ድግግሞሹ ደግሞ 5.86 እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ከቋንቋ አጠቃቀም እና ከስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ቀጥሎ ሶስተኛ ደረጃን የያዘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ ተጠኝ ተማሪዎች ከጻፉአቸው ድርሰቶች ውስጥ 577 ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 16.36% ይሆናል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑም 2.62 ሲሆን አማካይ ድግግሞሽ መጠኑ 3.27 ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተቀመጠው የስህተት ዓይነት ምድብ መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ሲሆኑ ይህም ከጠቅላላው 3526 ስህተቶች ውስጥ 112 የሚሆኑት በዚህ ምድብ ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ ይህ የስህተት ብዛት (መጠን) በመቶኛ ሲገለፅየስህተቶቹን ብዛት (መጠን) ለጠቅላላው የስህተቶች ብዛት በማካፍል የተገኘውን ውጠየት በመቶ በማባዛት የስህተቶቹን ብዛት (መጠን) በመቶኛ ለማውቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ የስህተት ብዛት በመቶኛ

ሲሰላ 3.18% ሲሆን በአንድ ድርሰተም የተገኘው አማካይ ስህተት ለማወቅ አማካይ የስህተት ብዛት (መጠን) ተጠኝ ተማሪዎች ለጻፉት አጠቃላይ ድርሰት በማካፈል የስህተት መጠኑ 0.51 ሆኗል፡፡በአንድ መቶ ቃላት በሚይዝ አንድ ድረሰት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማከፈል የተገኘው ውጤት በመቶ ተባዝቶ የስህተት ድግግሞሽ 0.64 እንደሆነ መረጃዉ ያሳያል፡፡

### 4.2.1. የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት

የቋንቋ አጠቃቀም ሲባል በድርሰት ውስጥ ያሉት ዐረፍተነገሮች የቋንቋን ህግ የጠበቁ ሆነው በቃላት አጠቃቀም ላይ የተለያዩ ስህተቶች የሚታዩባቸው ናቸው፡፡

ከሰንጠረዥ ሁለት መረዳት እንደሚቻለው ከአራቱ ዋና ዋና የስህተት ምድቦች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት በአጠቃላይ ከተገኙት 3526 ስህተቶች ውስጥ 1803 (51.13%) የሚሆነውን ስህተት የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ነው፡፡ አማካይ የስህተት ብዛቱ 8.2 ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ መጠኑ 10.23 ሆኗል፡፡

በዚህ አበይ የስህተት ምድብ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ንዑሳን የስህተት ምድቦች ፡- የሆሄያት ግድፈት፣ የሆሄያት ጭመራ ፣የሆሄያት ቅርፅና የቃላት አጠቃቀም ናቸው፡፡ ዝርዝር መረጃውን በሰንጠረዥ ሶስት እንደሚከተለቀው ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 3፦ በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት ዓይነቶች ዝርዝር መረጃ

| የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ |
| | ብዛት | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛትበቁጥር | በመቶኛ | | |
| የሆሄያት ቅርፅ | 667 | 71.88 | 0.06 | 7.62 | 641 | 73.26 | 5.83 | 7.26 | 1308 | 72.55 | 5.95 | 7.42 |
| የሆሄያት ግድፈት | 171 | 18.42 | 1.55 | 1.95 | 158 | 18.06 | 1.44 | 1.78 | 329 | 18.25 | 1.50 | 1.87 |
| የቃላት ድግግሞሽ | 55 | 5.93 | 0.5 | 0.63 | 45 | 5.14 | 0.41 | 0.51 | 100 | 5.55 | 0.45 | 0.56 |
| የሆሄያት ጭመራ | 35 | 3.77 | 0.32 | 0.40 | 31 | 3.54 | 0.28 | 0.35 | 66 | 3.66 | 0.3 | 0.37 |
| ድምር | 928 | 100 | 8.43 | 10.60 | 875 | 100 | 7.96 | 9.85 | 1803 | 100 | 8.20 | 10.23 |

### 4.2.1.1. የሆሄያት ቅርፅ

በሰንጠረዥ 3. እንደሚያመለክተው ተማሪዎች በፃፏቸው ሁለት ዙር ተከታታይ ድርሰት ውስጥ የሆሄያት ቅርፅ (አጣጣል) ለይቶ ባለ ማውቅ ምክንያት ብዙ ስህተቶች እንደተገኙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ከቀረቡት 1803 ስህተቶች ውስጥ 1308 የሚሆኑት የተፈፀሙት በዚህ ንዑስ የስህተት ምድብ ነው፡፡ የስህተቱ ብዛት በመቶኛ ሲቀመጥ 72.55 ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ ደግሞ 5.95 ሲሆን መቶ ቃላትን በያዘ አንድ ድርሰት ውስጥ ያለው ድግግሞሽ መጠን 7.42 መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የታዩት ስህተቶች የሆሂያትን ቅርፅ (አጣጣል) ባለማወቃቸው የተነሳ ሆሂያትን ቀያይሮ በመፃፍ እና የዲቃላ ሆሂያትን ከመደበኛው ሆሂያት ጋር ያላቸው ልዩነት ካለማወቅ ምክንያት በጥቅም ላይ በማዋላቸው የሚከሰቱ ስህተቶች ናቸው፡፡

በመቀጠልም ከድርሰቶቹ የተወሰዱትን ምሳሌዎች እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1. ያኣብሱማ በሂላዊ የጋብቻ ስርዓት...

2. ይህ ስግግር ተፈፃሚ የሚሆነው የሊጁ አባት ወይም አጉት ፍቃደኛ ከሆነ ቢቻ ነው፡፡

3. አፋሮች የራሳቸው ቃንቃ ፣ባሂልና ወጊ ያላቸው ህዝቦች ናቸው፡፡

4. ሁለቱ ተጋቢዎች አብረው ከኖሩ በሃላ በራሳቸው ፍላጉት የሚፈፀም ነው፡፡

በተራ ቁጥር 1 ለቀረቡት ምሳሌዎች የሚታዩት ስህተቶች ሆሄያትን በመለወጥ ሲሆን "ባህላዊ" በማለት ፋንታ ባሂላዊ፣የአብሱማ -- ያኣብሱማ ተብሎ ተፅፏል፡፡

ይህም ግዕዝ የነበረቸው |የ | ወደ ራብዕ |ያ| ሳድስ የነበረችው |ህ| ወደ ሳልስ |ሂ| በመለወጥ በፅህፈታቸው ውስጥ ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡

ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአፋርኛ የሆሄያት ስደራ ውስጥ ግዕዙና ሳድሱ ሆሄያት ባለመካተታቸውና በተጨማሪም "ሸ" የተባለችው ሆሄ ከነተወላጆቿ በአፋርኛ ቋንቋ የፊደል ስደራ ውስጥ አለመኖራቸው ነው (Loren F. Bliese (1981:1) ፡፡

ሁለተኛው ምሳሌ፡- በእድሜ ቢያንስም ሆነ ስማግሌ ቢሆን ኣብሱማ ስለሆነ የግድ ታገባዋለች፡፡ በዚህ አረፍተነገር ውስጥ ሽማግሌ ለማለት "ስማግሌ" በማለት ሳድሱን "ሸ" በ "ስ" ተቀይሯል፡፡ ምክንያቱም በአፋርኛ ቋንቋ የፊደል ስደራ "ሸ" የሚባለው የፊደል ዘር ባለመኖሩ "ሸ" ከማለት ይልቅ "ስ" ማለት ይቀላቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ለስህተት ተጋልጠዋል፡፡

በተራ ቁጥር 3 እና 4 የቀረቡት ምሳሌዎች እንደምንመለከተው ቋንቋ በማለት ፈንታ "ቃንቃ"፣ በኋላ በማለት ፈንታ "በሃላ" ብለው ፅፈዋል፡፡ይህ ስህተት የተፈጸመው የአማርኛ ቋንቋ ዲቃላ ሆሄያትን ቅርጽ ከመደበኛው ሆሄያት አለመለየትና ካለመረዳት የመነጨ ስህተት ነው፡፡

4.2.1.2. ግድፈት

በሰንጠረዥ 3 በሚታየው መረጃ መሰረት በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት የሆሄያት ግድፈት ነው፡፡ በተጠኚ ተማሪዎች ከተፈፀሙት 1803 የቋንቋ አጠቃቀም መካከል 329 የሚሆኑት በግድፈት የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ

18.25% ነው፡፡ አማካይ ስህተቱ 1.50 ሲሆን በመቶ ቃላት  በሚያዝ አንድ ድርሰት ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 1.87 እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

በጥናቱ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቱን ሲፅፉ መካተት ያለባቸው ነገሮች በመግደፍ በፅህፈት አማካኝነት በሚፈፀሙ ተግባቦቶች እንቅፋት ሊሆኑ ችለዋል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ተጠቅሰዋል፡፡ ግድፈት ያለበትን ቦታ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

1. ያ ኣፋር ብሄርሰብ የሚ( ) ረው በአፋር ኪልል ነው፡፡  በሰሜን ከኤ( )ትራ በምስራቅ ከጁቡቲ ጋር ይገ( )ኛል፡፡
2. ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻለው በቃላት መካከል ሆሂያትን በመግደፍ ስህተት ፈፅመዋል፡፡ የተገደፉት ሆሂያትም ኖ፣ ር እና ና ሲሆኑ የነዚህ ሆሄያት አለመኖር አረፍተነገሩን ውበትና ተነባቢነት እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡

ለምሳሌ በዚህ አረፍተነገር ውስጥ ያለውን ቃል ብናይ /ይገናኛል/ መሆን ሲገባው /ና/ ን በመግደፍ /ይገኛል/ የሚል ትረጉም በመስጠቱ አጠቃላይ የአረፍተነገሩ ትርጉም ክልሉ በምስራቅ ከጅቡቲ ጋር መገናኘቱ (አዋሳኝ) መሆኑን ሳይሆን በጅቡቲ ውስጥ እንደሚገኝ በማድረግ የታሰበውን ሃሳብ መግለፅ እንዳይችልና የትርጉም ለውጥ እንዲኖረው በማድረግ ስህተት እንደፈፀም ሆኗል፡፡

#### 4.2.1.3 የቃላት ድግግሞሽ /ድርታ/

በሰንጠረዥ 3 በቀረበው መረጃ መሰረት በቋንቋ አጠቃቀም አብይ የስህተት ምድቦች ከቀረቡት አራት ንዑሳን ምድቦች ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የቃላት ድግግሞሽ ነው፡፡ ድግግሞሹ ከጠቅላላ የስህተት ብዛት መቶ የሚሆነውን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም የስህተት ብዛት በመቶኛ ሲገለፅ 5.55% ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 0.45 ሆኗል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በተጠኚ ተማሪዎች በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ ቃላትን እየደጋገሙ የመጠቀም ችግር ተስተውሏል፡፡ ይህን አስመልክተው ሰለሞን ሐለፎም (1997፣92) አንድን ቃል በአንድ አረፍተነገር ውስጥ እንዳሰኘን መዝራት ሀሳቡን ያደበዝዘዋል፤ የአረፍተነገሩን ውበት ይቀንሰዋል፤ መልዕክቱ በቀጥታ እንዳይተላለፍም እንቅፋት ይሆናል በማለት ገልፀዋል፡፡ በተማሪዎቹ ፅሁፍ ውስጥም የተከሰተው ችግር ይሄ ነው፡፡ ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1. ሁላችን እንደምናወቀው ባእላት በማህበረሰባችን ዘንድ ባእላት ትልቅ ቦታ ያላቸው አመታዊ ክስተቶች ናቸው፡፡
2. ለብአል ማድመቂያ የሚሆኑ አዳዲስ መጋረጃዎች፣ አዳዲስ ምንጣፎች፣ አዳዲስ ጫማዎች እና አዳዲስ ጌጣጌጦች ይገዛሉ፡፡
3. ኢትዩጽያ ስንት እና ስንት ማዕድናት እያላት፣ ስንትና ስንት የእርሻ መሬት እያላት፣ ስንት እና ስንት የተፈጥሮ ነዳጅ እያላት እንኳንስ ደሃ ልትባል ቀርቶ ለውጭም የሚበቃ ምርት የማምረት አቅም አላት፡፡

ከላይ የቀረበው ምሳሌ እንደሚያሳየው በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሰመረበት የቃላት ድግግሞሽ (ድረታ) የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ስህተት ሊፈጠር ችሏል፡፡ ተስተካክሎ ሲፃፍም፡-

1. ሁላችን እንደምናውቀው ባእላት በማህበረሰባችን ዘንድ ትልቅ ቦታ ያላቸው አመታዊ ክስተቶች ናቸው፡፡
2. ለባእል ማድመቂያ የሚሆኑ አዳዲስ መጋረጃዎች፣ ምንጣፎች፣ ልብሶችና ጌጣጌጦች ይገዛሉ፡፡
3. ኢትየጵያ ስንት እና ስንት ማዕድናት፣ የእርሻ መሬት እና የተፈጥሮ ነዳጅ እያላት እንኳን ደሃ ልትባል ቀርቶ ለውጭም የሚበቃ ምርት የማምረት አቅም አላት፡፡ በማለት ቢስተካከል አረፍተ ነገሩም ሆነ ሃሳቡ የተቃና ሊሆን ይችላል፡፡

### 4.2.1.4. የሆሄያት ጭመራ /እከላ/

ከሰንጠረዥ 3 መረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ አጠቃቀም አብይ የስህተት ምድቦች መካከል ከቀረቡት አራት ንዑሳን ምድቦች ውስጥ በአራተኛ ደረጃ የተቀመጠው የሆሄያት ጭመራ (እከላ) ነው፡፡ ጭመራው (እከላው) ከጠቅላላው የስህተት ብዛት 66 የሚሆነውን የሚሸፍን ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲገልፅ 3.66% ይሆናል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑም 0.3 ይደርሳል፡፡ የስህተት ድግግሞሹ 0.37 እንድሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

ከላይ ሰንጠረዡ እንደሚያመለክተው በተጠኚ ተማሪዎች በተፃፉ ድርሰቶች ውስጥ ቅጥያዎችን እየጨመሩ የመፃፍ ችግር ተስተውሏል፡፡ ይህም በምሳሌ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ከመምህራንኖች ጋር እሰጣ አገባ ውስጥ ሲገቡና ለትምህርት መጥፎ አመለካከት ሲኖራቸው እንመለከታለን፡፡

ከላይ በቀረበው አረፍተነገር ውስጥ ስህተቱ ሊከሰት የቻለው "መምህራን" በራሱ ብዙ ቁጥር አመልካች ያለው ሆኖ እያለ "ኖች" የተባለውን አላስፈላጊ ቅጥያ በመጨመር ወይም በማከል ስህተት ሊፈፀም ችሏል፡፡ ተስተካክሎ ሲፃፍም ከመምህራን ጋር እሰጣ አገባ ውስጥ ሲገቡና ለትምህርት መጥፎ አመለካከት ሲኖራቸው እንመለከታለን፡፡ በማለት ቢስተካከል አረፍተነገሩ የተቃና ይሆናል፡፡

### 4.2.2. የቋንቋ አወቃቀር

በሠንጠረዥ 2 ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በአብይ ምድብ ከተዘረዘሩት አራት የስህተት አይነቶች መካከል በስህተት ብዛቱ በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው፡፡ ይህ የስህተት ምድብ በአጠቃላይ ካሉት 3526 ስህተቶች መካከል 577 ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ይህም ቁጥር በመቶኛ ሲቀመጥ  የስህተቶችን ብዛት(መጠን) ለጠቅላላው የስህተቶች ብዛት በማካፈል የተገኘው ውጤት በመቶ ተባዝቶ16.36%  ሊሆን ችሏል፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑን ለማገኘት አማካይ የስህተት መጠን (ብዛት) ለተጠኝ ተማሪዎች ለጻፉት አጠቃላይ ድርሰት በማካፈል 2.62 ሆኖአል፡፡  የሚሆነው ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም ቁጥር በመቶኛ ሲቀመጥ  ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑም 2.62 ይሆናል፡፡ በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ ለማወቅ  ደግሞ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈል  የተገኘውን ውጤት በመቶ በማባዛት የድግግሞሽ መጠኑ 3.27 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ ሶስት ንዑሳን የስህተት አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ፡- የቃላት አጠቃቀም፣ የአረፍተነገር ስምምነት እና የመስተዋድድ አገባብ ናቸው፡፡ ዝርዝር መረጃውን በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## ሰንጠረዥ 4፡- በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መረጃ

| የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ |
| | ብዛትበ ቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመ ቶኛ | | |
| የቃላት አጠቃቀም | 81 | 26.82 | 0.74 | 0.93 | 79 | 28.72 | 0.72 | 0.89 | 160 | 27.73 | 0.72 | 0.90 |
| የአረፍተነገር ስምምነት | 170 | 56.29 | 1.55 | 1.95 | 157 | 57.09 | 1.43 | 1.37 | 327 | 56.67 | 1.49 | 1.86 |
| የመስተዋድድ አገባብ | 51 | 16.89 | 0.46 | 0.58 | 39 | 14.18 | 0.35 | 0.43 | 90 | 15.60 | 0.41 | 0.51 |
| ድምር | 302 | 100 | 2.75 | 3.46 | 275 | 100 | 2.5 | 3.09 | 577 | 100 | 2.62 | 3.27 |

### 4.2.2.1. የቃላት አጠቃቀም

በቋንቋ አወቃቀር ከተመደቡት አራት ንዑሳን የስህተት አይነቶች ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ በሠንጠረዥ 4 ቀርቧል፡፡

በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ 160 የሚሆኑ ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ በመቶኛ ሲቀመጥ 27.73% ነው፡፡ በአንድ ድርሰት ውሰጥ የሚገኘው አማካይ ስህተት 0.72 ሲሆን በአንድ መቶ ቃላት ያለው ድርሰት የድግግሞሽ መጠን 0.90 ሆኗል፡፡ በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ በተገኙ ስህተቶች ማየት የተቻለው ችግር በአረፍተነገር ምስረታ ወቅት ቃላትን ተገቢ በሆነ ቦታ አለመጠቀም ነው፡፡ የሚከተሉት ምሳሌዎች ለአብነት ቀርበዋል፡፡

1. ለባእል ማድመቂያ የሚሆኑ አዳዲስ መጋረጃዎች ፣አዳዲስ ልብሶች፣ አዳዲስ ጫማዎችእና ጌጣጌጦች ይገዛሉ፡፡
2. ባለፉት ተከታታይ ሁለትና ሶስት አመት …

ከላይ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደምንረዳው በተራ ቁጥር1 ላይ የቃላት አላስፈላጊ ድግግሞሽ የታዩ ሲሆን በተራ ቁጥር 2 ደግሞ አመታት በሚል ፈንታ አመት በማለት አላስፈላጊ የሆነ የቃላት አጠቃቀም ይህም አመታት የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን

አመት የሚለው ቃል ደግሞ ነጠላ ቁጥርን ይገልፃል፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ ይህ ስህተት ሊከሰት ችሏል፡፡

#### 4.2.2.2. የአረፍተነገር ስምምነት ስህተት

ከሠንጠረዥ 4 በተገኘው መረጃ መሰረት በቋንቋ አወቃቀር ስህተት መካከል ከተዘረዘሩት አራት ንዑሳን የስህተት አይነቶች ውስጥ ቀዳሚውን ደረጃ የያዘው የአረፍተነገር ስምምነት ስህተት ነው፡፡ ይህም በቋንቋ አወቃቀር ምድብ ከ577 ስህተቶች ውስጥ 327(156.67%) ያህል የሚሆነው የስህተት ብዛት የተገኙበት ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.49 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 0.90 እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል፡፡ በዚህ ክፍል የተፈፀሙ ስህተቶች የቁጥር ፣የፆታ ስምምነት አለመኖርና የአረፍተነገር ስምምነቱ መፋለስ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ይህም ለአብነት ያህል ለማሳየት ተሞክሯል፤ ስህተቱ የተፈፀመበት ቦታ ላይም ተሰምሮበታል፡፡

1.በእስልምና እምነት ተከታታይ ባእላት መካከል አንዱ <u>ኢ.ድ</u> ናቸው፡፡ የዚህ አረፍተነገር ግስ የሚያመለክተው ብዙ ቁጥር ነው፡፡ ይሁን እንጅ የሚነገረው ግን በነጠላ ቁጥር ለቀረበው ቃል ኢ.ድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተናጋሪው ሀሳቡና ስለእሱ የሚገልፀው ግስ በቁጥር አልተጣጣመም፡፡ አንዱ ነጠላ ሌላው ብዙ ነው፡፡ ግሶችን በነጠላ ቁጥር "ነው" በማለትና በማቅረብ ችግሩን ማቃለል ይቻላል፡፡ ይህም የእስልምና እምነት ተከታዮች ከሚጠብቁት ባእላት መካከል አንደኛው ኢ.ድ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ማስተካከል ይቻላል፡፡

2. <u>ሰዎቹ</u> ባእሉ ከመድረሱ በፊት ዝግጅቱ <u>ጀመረ</u>፡፡ የዚህ አረፍተነገር ችግር ባለቤትና ግሱ አልተጣጣመም ነው፡፡ ምክንያቱም ባለቤቱ ብዙ ቁጥር ሲሆን ግሱ ደግሞ ነጠላ ቁጥርን በመግለፁ ለስህተት ተዳርጓል፡፡

#### 4.2.2.3. የመስተዋድድ ስህተት

በቋንቋ አወቃቀር ዋና የስህተት ምድብ ውስጥ በስህተት ብዛት በሁለተኛ ደረጃ ከተገለፀው የቃላት አወቃቀር ቀጥሎ የምናገኘው የመስተዋድድ አገባብ ስህተት ነው፡፡ በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ 90 የሚሆኑ ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ ይህ ቁጥር በመቶኛ ሲገለፅ 15.60% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ 0.41 ነው፡፡ የስህተት ድግግሞሽም 0.41 ደርሷል፡፡ የታዩትም ስህተቶች መስተዋድዶችን ተገቢ ባልሆነ ቦታ በመጨመርና በመግደፍ

የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው ስህተቶችም እንደሚከተለው በምሳሌ ቀርቧል፡፡ በስህተቶችም ላይ አግዳሚ መስመር ተሰምሮ ይገኛል፡፡

1. ሁለተኛው ባህላዊ ከጋብቻ አይነት የካታል ወይም በፍላጉት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡
2. ለቻት መግቻ ገንዘብ ከጠፋ--- ዝርፊያ ይሰማራል፡፡

እንዚህን አረፍተነገሮች እንደሚከተለው ተስተካክለው ቀርበዋል፡፡

1. ሁለተኛው ባህላዊ ጋብቻ አይነት "የካታል" ወይም በፍላጉት ላይ የተመሰረት ነው፡፡
2. ለጫት መግዣ ገንዘብ ከጠፋ ወደ ዝርፊያ ይሰማራል፡፡

4.2.2.4. **የጾታ፣ የመደብና የቁጥር ስምምነት**

በአረፍተነገር ውስጥ የሚታዩት ሰዋሰዋዊ ችግሮች ሲሆኑ በዋናነትም ባለቤትና ግስ አለመስማማት ይታያል፡፡ በተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶችም ውስጥ ይህ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ምሳሌውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. መምህር ብሆን ለተማሪ ተምሳሌት እሆን ነበርን፡፡ የዚህ አረፍተነገር ባለቤት "መምህር" የሚለው ቃል የተገለፀው በነጠላ ቁጥር ነው፡፡ አንደኛ መደብ "እኔ" በሚል የተገለፅ ሲሆን ግሱ ደግሞ የሚያሳየው "ነበርን" የሚል ብዙ ቁጥር በአንደኛ መደብ "እኛ" በሚለው ተገጸዋል፡፡ ስለዚህ የባለቤትና የግስ ስምምነት የለም፡፡መሆን የነበረበት፡-

- መምህር ብሆን የተማሪ ተምሳሌት እሆን ነበር፡፡ በማለት ማስተካከል ተችሏል፡፡

2. መምህር ብሆን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ጎበዝ እንዲሆኑ ምክር በመስጠት ፣በትርፍ ጊዜ በማስተማር ፣ከተማሪ ወላጆች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና ክትትል በማድረግ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የራስን ጥረት ታደርጊያለሽ፡፡ በዚህ አረፍተነገር ውስጥ "መምህር" የሚለው ቃል የአረፍተነገር ባለቤት ነው፡፡ጾታውም ተባእታይ ሲሆን ግሱ ደግሞ የተገለፀው በአንስታይ ፆታ "ታድርጊያለሽ" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ አረፍተነገሩ የጾታ ስምምነት ችግር እንዳለበት ያሳያል፡፡

   ተስተካክሉ ሲፃፍም፡-

መምህር ብሆን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ምክር በመስጠት ፣በትርፍ ጊዜ በማስተማር ፣ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና ክትትል በማድረግ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዝግቡ የራሴን ጥረት አደርጋለሁ፡፡ በሚል ሊስተካከል ይቻላል፡፡

### 4.2.3. የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም

ስርዓተ ነጥቦች እንደ ቃላት ፣ሀረጋትና አረፍተነገሮች ሁሉ የሀሳብና የስሜት ወካይ ናቸው፡፡ አገልግሎታቸውም ሀሳብን ፣ስሜትን ወዘተ በጥቅሉ መልእክቱን ጸሀፊው ለአንባቢው ወይም ለአድማጩ ግልፅና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ሲችል ነው፡፡በመሆኑም መልእክትን ግልፅና ግብ መች በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ በሚዋቀረው አረፍተነገር ውስጥ ተገቢ የሆነውን የነጥብ ስርዓት በተገቢ አገባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ጥናት በስህተት ከታዩት የስህተት ምድቦች ውስጥ ከቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ ከሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት በአጠቃላይ ከተገኙት 3526 ስህተቶች ውስጥ 1034 (29.33%) የሚሆነውን ስህተት የያዘው የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ነው፡፡ በዚህም የስህተት ምድብ አማካይ የስህተት ብዛት 4.7 ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ መጠኑ ድግሞ 5.86 ሆኗል፡፡ ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ በብዛት የታዩት አራት ነጥብ፣ ድርብ ሰርዝ ፣ነጠላ ሰርዝ ፣ይዘት እና ቅንፍ ናቸው፡፡ ዝርዝር መረጃው በሰንጠረዥ 5 ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 5፡- በሰርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ የስህተት አይነቶች ዝርዝር መረጃ

| የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ |
| | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛትበቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | |
| አራት ነጥብ | 170 | 32.13 | 1.54 | 1.93 | 168 | 33.26 | 1.52 | 1.88 | 338 | 32.7 | 1.54 | 1.92 |
| ነጠላ ሰርዝ | 104 | 19.66 | 0.95 | 1.19 | 99 | 19.60 | 0.9 | 1.11 | 203 | 19.63 | 0.92 | 1.15 |
| ድርብ ሰርዝ | 96 | 18.15 | 0.87 | 1.09 | 85 | 16.83 | 0.77 | 0.95 | 1.81 | 17.50 | 0.82 | 1.02 |
| አንድነጥብ (ይዘት) | 152 | 28.73 | 1.4 | 1.76 | 148 | 29.30 | 1.34 | 1.65 | 300 | 29.01 | 1.4 | 1.74 |
| ቅንፍ | 7 | 1.32 | 0.06 | 0.07 | 5 | 0.99 | 0.05 | 0.06 | 12 | 1.16 | 0.05 | 0.06 |
| ድምር | 529 | 100 | 4.80 | 6.03 | 505 | 100 | 4.59 | 5.68 | 1034 | 100 | 4.7 | 5.86 |

### 4.2.3.1. የአራት ነጥብ አጠቃቀም

ሰንጠረዥ 5 እንደሚያመላክተው በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከተዘረዘሩት መካከል ብዙውን ቁጥር የያዘው የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት እንደሆነ መረጃው ያሳያል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ከታዩት 3,526 ስህተቶች መካከል 338 የሚሆኑት በዚህ ምድብ ውስጥ ይገኛሉ።ይህም በመቶኛ ሲቀመጥ 32.7% ሲሆን አማካኝ ስህተቱ 1.54 ሆኗል።በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኙት የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 1.92 ነው።

አራት ነጥብ በአንድ አረፍተነገር ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን ሙሉ ሀሳብ መጠቃለሉን ለማመልከት የሚያገለግል ቢሆንም በድርሰቶቹ ውስጥ ባሉት አረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ በታዩት ስህተቶች አራት ነጥብ በትክክል በተገቢው ቦታ አለመጠቀም መቻሉ ነው።ለናሙና ከቀረቡት ምሳሌዎች ስርአተ ነጥቦቹ በትክክለኛው ቦታቸው ያልገቡበትን ቦታ በቅንፍ ለማሳየት ተሞክሯል።

ጦርነቱ ብዙ ችግሮችን አስከትሏል ( ) ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ተከታተሰይ አመት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት የህዝብ መገልገያ ከሆኑ መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት፡ ትምህርት ቤቶች ፡ባንኮችና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል (. ) በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ ለችግር ተጋልጧል(፤)

ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ በመጀመሪያው አረፍተነገር አራት ነጥብን በተገቢው ቦታው ያለማስቀመጥ፤በሁለተኛው አረፍተነገር ላይ አንድ ነጥብ (ይዘትን) በመጠቀም፣በሶስተኛው አረፍተነገር ደግሞ ድርብ ሰረዝን በመጠቀም የተፈፀሙ ስህተቶች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል።

በመሆኑም እነዚህ ስህተቶች በተፈፀሙበት ቦታ ላይ አራት ነጥብን ተክቶ በማስገባት እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል።

ጦርነቱ ብዙ ችግሮችን አስከትሏል። ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ተከታታይ አመታት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት የህዝብ መገልገያ ከሆኑት መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ባንኮችና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል። በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ ለችግር ተጋልጧል፡፡

### 4.2.3.2. የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም

በዚህ ንኡስ የስህተት ምድብ ከአጠቃላይ የስህተት ብዛት ውስጥ 203 የሚሆኑ ስህተቶች ታይተዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 19.63% ሆኗል።በአንድ ድረሰት ውስጥ ያለው አማካኝ የስህተት ብዛት 0.92 ሲሆን በአንድ መቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የድግግሞሽ መጠን ደግሞ 1.15 ደርሷል።

ይህ ስርአተ ነጥብ በአንድ አረፍተነገር ውስጥ ከአንድ መመዘኛ አንፃር ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የሚገልፁ ቃላትን እና ሀረጋትን ወዘተ..... ለመለየት የሚያገለግል ቢሆንም በስርአተ ነጥቡ አጠቃቀም ዙሪያ የታዩ ችግሮች ተስተውለዋል።ነጠላ ሰረዙ ለምን ግልጋሎት መዋሉን እና ከሌሎች ጋር ያለውን ልዩነት ባለማወቅ በሁለት ነጥብ የመተካት ሁኔታ ይታያል።ለምሳሌ ያህልም እንደሚከተለው ቀርቧል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት የህዝብ መገልገያ ከሆኑት መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት(:) ትምህርት ቤቶች(፡) ባንኮችና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መገንዘብ የተቻለው ነጠላ ሰረዙ ለምን ግልጋሎት መዋል እንዳለበት እና ከሌሎች ስርአተ ነጥቦች ጋር ያለውን ልዩነት ባለዋወቅ በነጠላ ሰረዙ ፈንታ ሁለት ነጥብ በመተካት ስህተት ሊፈፀም ችሏል።በመሆኑም ከላይ በቀረቡት አጠቃቀሞች የተነሳ የተፈፀመውን ስህተት ነጠላ ሰረዙን በማስገባት በሚከተለው መልክ ማስተካከል ይቻላል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት የህዝብ መገልገያ ከሆኑት መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ባንኮችና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል።

#### 4.2.3.3. የድርብ ሰረዝ አጠቃቀም

በዚህ ንኡስ የስህተት ምድብ በድረሰቶቹ ውስጥ ከተፈጸሙት ጠቅላላ ስህተቶች ውስጥ 181 የሚሆነው በዚህ ምድብ ውስጥ ተገኝቷል።ይህም የስህተት ብዛት በመቶኛ ሲሰላ 17.50 ይሆናል።አማካኝ የስህተት መጠኑ 0.82 ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ ያለው የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 1.02 ሆኗል።በዚህ ስርአተ ነጥብ ምክንያት ከታዩ ስህተቶች እንደሚከተለው በምሳሌ ቀርቧል።

ባአብሱማ የምታገባ ልጃገረድ በሰርጋ እለት ሰርገኛው ከመምጣቱ በፊት ልብሷን ትለብሳለች (።) አይኗን ትካካላለች (።) የሚያውድ ሽቶም በመቀባት ከጋደኞቿ ጋር ሆና ሙሽራውን መምጣት ትጠባበቃለች (፤)

ድርብ ሰረዝ እራሳቸውን ችለው በማሰሪያ አንቀፅ ሊወሰኑ የሚችሉ ነገር ግን የሀሳብ ዝምድና ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ለመለየት የሚያገለግል ቢሆንም ከዚህ በላይ በምሳሌው በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ድርብ ሰረዝ በተገቢው ቦታው አለመቀመጥ እና በአራት ነጥብ የመተካት ስህተት ተፈፅሞ ይታያል።ስለዚህ ከላይ በተገለፁት አጠቃቀሞች ምክንያት የተከሰቱትን ስህተቶች ማስተካከል ይቻል ዘንድ አራት ነጥቡን አስወግዶ ድርብ ሰረዙን

መተካት በተጨማሪም ድርብ ሰረዙን አላስፈላጊ ከሆነ ቦታ በማንሳት እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል።

ባአብሱማ የምታገባ ልጃገረድ በሰርጓ እለት ሰርገኛው ከመምጣቱ በፊት ልብሷን ትለብሳለች ፤አይኗን ትኳኳላለች፤ የሚያውድ ሽቶም በመቀባት ከጓደኞቿ ጋር ሆና ሙሽራው መምጣቱን ትጠባበቃለች።

#### 4.2.3.4. ቅንፍ

በሰንጠረዥ አምስት  በቀረበው መረጃ መሰረት በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ከቀረቡት አራት ንኡሳን ምድቦች ውስጥ በአራተኝነት ደረጃ የተቀመጠው የቅንፍ ስህተት ነው።
ቅንፍ ከጠቅላላው የስህተት ብዛት 12 በመቶኛ ሲገለፅ 1.16 ሆኗል።አማካኝ የስህተት ብዛቱ 0.05 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 0.06 እንደሆነ ያመለክታል።

ቅንፍ በአረፍተነገር ውስጥ ከሚገቡ የውጭ ወይም ያልተለመዱ ወይም በሚፃፈው ቋንቋ ተናጋሪ ዘንድ በአገባባቸው ሆነ በፍቻቸው የማይታወቁ ቃላትን አቻ ፍች ለማመልከት ያገለግላል።በመሆኑም በዚህ የስርአተ ነጥብ ምክንያት የሚከሰቱ ስህተቶች እንደሚከተለው በምሳሌ ቀርበዋል።

በባእል ቀንም በጠዋት ተነስቶ ኢ.ድ ቦራ ወደ ፀሎት ስፍራ በመሄድ የኢ.ድ ሶላት ስግደት ይከናወናል።
ከላይ በምሳሌው የተገለፀው ስርአተ ነጥቡ መግባት ባለበት ቦታ ላይ መግባት አለመቻሉ የቃላቱን ትርጉም በግልፅ አለማስቀመጥ አለመቻል ስህተት ተፈፅሟል።ስለዚህ ሲስተካከል በባአል ቀንም በጠዋት ተነስቶ ኢ.ድ ቦራ (ፀሎት ቦታ) በመሄድ የኢ.ድ ሶላት (ስግደት) ይከናወናል።

#### 4.2.3.5. አንድ ነጥብ (ይዘት)

በዚህ ንኡስ የሰህትት ምድብ በተማሪዋቹ ድርስቶች ውስጥ ከተፈፀሙት ከጠቅላላ  ስትቶች ውስጥ 300 የሚሆነው በዚህ ምድብ ውስጥ ተገኝተዋል ፡፡ ይህም የስህተት ብዛት በመቶኛ ሲሰላ 29.01 ሆኗል ፡፡ አማካኝ የስህተት መጠኑ 1.4 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ

1.74 ነው፡፡ በዚህ ስረአተ ነጥብ ምክንያት የተፈጸሙ ስህተቶች ለአብነት ያህል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. ጦርነቱ የህዝብ መገልገያ ከሆኑት መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት ትምህርት ቤቶች ባንኮች እና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል (.)

ከላይ በምሳሌ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡት አንድ ነጥብ(<u>ይዘት</u>) በአራት ነጥብ ፈንታ_በመግባት በድርሰቶች ውስጥ ስህተት ፈጥረዋል ፡፡ ይህ ከላይ በተራ ቁጥር 1 የቀረበው ኢ.ነገር ተስተካክሎ ሲፃፍ

1 ጦርነቱ የህዝብ መገልገያ ከሆኑት መሰረተ ልማቶች መካከል የጤና ተቋማት ትምህርት ቤቶች ባንኮች እና የግለሰብ ሱቆች ሳይቀሩ ተዘርፈዋል፡፡

በአጠቃላይ ስርአተ ነጥቦች በትክክለኛ ቦታ መጠቀም ካልተቻለ ለጽሁፍ ተግባቦት ተፅኖ ያሳድራል ፡፡

### 4.2.4. መለየት ያልተቻሉ የስህተት ዓይነቶች

**ሰንጠረዥ 6፡- መለየት ያልተቻሉ የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀሙ ስህተቶች**

| የስህተት ዓይነቶች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት | | አማካይ ስህተት | አማካይ የስህተት ድግግሞሽ |
| | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመ ቶኛ | | | ብዛት በቁጥር | በመቶኛ | | |
| | 62 | 3.40 | 0.56 | 0.70 | 50 | 2.75 | 0.45 | 0.55 | 112 | 6.6 | 0.51 | 0.62 |

በሰንጠረዥ ሁለት መረዳት እንደሚቻለው ከአራቱ የስህተት ምድቦች መካከል የመጨረሻውን ደረጃ የያዘው መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች እንደሆኑ መረጃው ያመልከታል፡፡ በዚህ መሰረት በአጠቃላይ ከተገኙት 3526 ስህተቶች ውስጥ 112 /3.18%/ የሚሆነው ስህተት የተገኘው በዚህ ምድብ ውስጥ ነው፡፡ አማካይ የስህተት ብዛቱም 0.51 ሆኗል፡፡ የስህተት ድግግሞሽ መጠኑ 0.64 ነው፡፡ ይህ የስህተት አይኑት እንደሌሎች ንዑሳን የስህተት አይነት መድቦች የሌሉት ሲሆን እንደሌሎችም የስህተት አይነቶች ሊቆጠርበት የቻለበት ምክንያት በቀላሉ ስህተቶችን ለይቶ ለማውጣት በማያስችል ሁኔታ ተዘበራርቀው በመገኘታቸው ነው፡፡

ለምሳሌ ያህልም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በኢ.ድ አከባበር ጊዜ የሚናድርጐ በአንደኛ ደረጃ ደባቆሎ አቀራተሎው ከዚሚ በቅትሎ ልበሰ ኦተት በሌ ቀጥየ ቤቴን ከዛ አፀዳለሁ…

  ከዚህ በላይ በምሳሌነት የቀረበው ፅሁፍ ውስጥ የቀረቡት ስህተቶች እንደሚያሳዩት አረፍተነገሮቹ መቋጫ የሌላቸውና ውስብሰብ ያሉ የቃላት ስብሰብ በመሆናቸው የስህተት አይነቶችን ለይቶ ለማውጣት ችግር ነው፡፡ በመጀመሪያውና በሁለተኛው መስመር የተፃፉትን ፅሁፎች ስናይ የኢ.ድ በዓል ከመድረሱ በፊት ያሉትን ቅድመ ዝግጅቶች ለመግለፅ የተፈለገ ይመስላል፡፡ ይህን ሀሳብ ለመግለፅ መሆን ያለበት :-
- በኢ.ድ አከባር ጊዜ የምናደርገው በመጀመሪያ ደረጃ ዳቦቆሎ እቆርጣለሁ፤ልብስ አጥባለሁ፤ በመቀጠልም ቤቴን አፀዳለሁ፡፡" ተብሎ ቢፃፍ የተሻለ አገላለፅ ይሆን ነበር፡፡

## 4.3. የስህተት ምንጭ

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ይህ የስህተት ምንጭ ትኩረት የሚደረገው ሶስተኛውን መሰረታዊ የጥናት ጥያቄ ለመመለስ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ተጠኚ ተማሪዎች በፃፉቸው ድርስቶች ውስጥ የፈፀሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ አማካኝነት ከተተነተኑ እና ተተንትነውም የስህተት ድግግሞሽ ከታወቀ በኃላ ለስህተቶችም መከሰት መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች ማመልከት ነው፡፡ በመሆኑም በተጠኚ ተማሪዎች ድረስቶች ከተፈፀሙ ስህተቶች ትንተና፣ከመምህራንና ከተማሪዎች መጠይቅ ምላሾች ከሌሎችም ተዛማጅ ፅሁፍ ከተሰበሰቡ መረጃዎች አገናዝቦ በመውሰድ በዋናነት የታዩት የስህተት ምንጮች :-

1. ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ
2. አፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ
3. የማስረፅ ስልት ተፅእኖ
4. ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ
5. የአማርኛ ቋንቋ ድምፀ ልሳናት ተፅዕኖ ናቸው፡፡

## 4.3.1. ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

ውስጠ ቋንቋ ተፅኖ በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ ለተፈፀሙ ስህተቶች የስህተት ምንጭ መካካል አንዱ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋቸውን አዲስ ስርአት ከለመዱ በኋላ ህጉን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል በመረዳት ለመናገርና ለመፃፍ በሚያደርጉት ሙከራ የተፈጸመ ስህተት ነው፡፡

በመሆኑም ተማሪዎቹ ለዚህ ስህተት የተጋለጡት ባልተሟላ ትምህርት፣ የቃላት ድግግሞሽና በተሳሳተ ማጠቃለያ ምክንያት እንደሆነ በተዛማች ፅሁፍ ላይ ቀርቧል፡፡

ስህተቶቹም፣ በቋንቋ አጠቃቃም የስህተት አይነት ምድብ ስር ካሉት ንኡሳን ስተቶች መካካል ባልተሟላ ትምህርት የተነሳ የሆሄያት ቅርጽ (አጣጣል) ባለመለየት ምክንያት አላግባብ እንደሚጠቀሙ ለመገዘብ ተችሏል፡፡ለአብነት ያህልም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- <u>ያአፋር</u> ብሄረሰብ የሚኖረው በአፋር <u>ኪልል</u> ነው፡፡

በዚህ በቀረበው አረፍተነገር የታዩት ስህተቶች የሆሄያት ቅርፅ ወይም አጣጣል በትክክል ባለማወቅ ሆሄያትን በመለወጥ(በመተካት) የተፃፉ ስህተቶች ሲሆኑ /የአፋር/ በማለት ፈንታ /ያአፋር/ እና /ክልል/ በማለት ፈንታ /ኪልል/ ተብሎ ተለውጦ ተፅፏል፡፡ ይህም ግዕዝ የነበረውን/የ/ ወደ ራብዕ /ያ/ እና ‹‹ክ››ን በ‹‹ኪ›› በመተካት በፅህፈታቸው ውስጥ ስህተት ሊፈፅሙ ችለዋል፡፡ ይህም ባልተሟላ ትምህርት የተነሳ የተከሰተ ስህተት ነው፡፡

- በእድሜ ቢያንስም ሆነ <u>ስማግሌ</u> ቢሆን <u>አብሱማ</u> ስለሆነ የግድ ታገባዋለች

በዚህ አረፍተነገር ውስጥ ሽማግሌ ለማለት <u>ስማግሌ</u> ሳድሱን ‹‹ሽ›› ን በ‹‹ስ›› ተቀይሯል፡፡ ምክንያቱም ‹‹ሽ›› የሚባለው ሆሄ ከነተወላጆቹ ባለመኖሩ ለስህተት ተዳርገዋል፡፡ በተጨመሪም በተግባር እንደታየው በአንደበታቸው ‹‹ሽ›› ከማለት ይልቅ ‹‹ስ›› ማለት ይቀላቸዋል፡፡

የሆሄያትን ቅርፅ ወይም አጣጣል ባለማወቅና አላግባብ በመጠቀም በጽሁፋቸው ላይ በቃላትም ሆነ በመስተዋድዶች ላይ የቃላት ድግግሞሽ በማስገባትና ቦታ ቅየራ በማድረግ ስህተት ይፈፅማሉ፡፡ ከነዚህ ስህተቶች በተጨማሪ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲፅፉ በቃላት አጠቃም (ድግግሞሽ) የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶችም አሉ፡፡ ስህተቶቹም በአንድ አረፍተነገር ውስጥ ቃላትን እየደጋገሙ የመጠቀም ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

- ኢትዮጰያ ስንትና ስንት ማእድናት እያላት፣ስንትና ስንት የእርሻ መሬት እያላት፣ ስንትና ስንት የተፈጥሮ ሀብት እያላት ...

ከላይ የቀረበውን ምሳሌ ተስተካክሎ ሲፃፍ ኢትዮጵያ ስንትና ስንት ማእድናት፣ የእርሻ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብት እያላት... ተብሎ መፃፍ ሲገባው አላስፈላጊ የሆኑ ቃላት አጠቃቀም (ድረታ) በመጠቀም የአረፍተነገሩን ተነባቢነት ከመቀነሱም ባሻገር ውበቱም እንዲደበዝዝ እና መልክቱ በቀጥታ እንዳይተላለፍ እንቅፋት በመሆን በፅሁፋቸው ውስጥ ስህተት እንድፈፅሙ ሊያደርግ ችሏል፡፡

ሌላው በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የምናገኘው የስህተት አይነት የመስተዋድድ ስህተት ሲሆን ይህም በተማሪው ድርሰት ውስጥ ለስህተት የሚያጋልጣቸው ነው፡፡ ለአብነት ያህልም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የአፋር ብሄረሰብ ሁለት የባህላዊ የጋብቻ አይነቶች አሏቸው፡፡
- ለጫት መግዣ ገንዘብ ከጠፋ (      ) ይሰማራል፡፡

በመጀመሪያው አረፍተነገር የአፋር ብሄረሰብ ሁለት ባህላዊ የጋብቻ አይነቶች አሏቸው፡፡ መሆን ሲገባው ባህላዊ ከሚለው ቃል በፊት ቀድማ የገባቸው ‹‹የ›› ተገቢ ባልሆነ ቦታ በመጨመር የተፈፀመ ስህተት ነው፡፡ በሁለተኛው አረፍተነገር ደግሞ ‹‹ወደ››የሚለውን መስተዋድድ በመግደፍ አረፍተ ነገሩ ውበት ከማጣቱም በላይ ሀሳብ የመግልፅ አቅሙ ደካማ አድረጎታል፡፡

በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምድብ ውስጥ የተፈፀመው የስህተት አይነት ምድብ አንዱ የአረፍተነገር ስምምነት ነው ፡፡ ይህም በፆታ፣ በመደብ በቁጥር አለመስማማት የተነሳ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ይህ ችግር ይስተዋላል፡፡ እነዚህ ስተቶች ለመገኘታቸው ምክንያት የሚሆነው ያልተሟላ ትምህርት ሊሆን ይችላል፡፡ ምሳሌውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- መምህር ብሆን ለተማሪ ተምሳሌት እሆን ነበርን፡፡

የዚህ አረፍተነገር ባለቤቱ ‹መምህር› የሚለው ቃል የተገለፀው በነጠላ ቁጥር አንደኛ መደብ ‹‹እኔ›› በሚል የተገለፀ ሲሆን ግሱ ደግሞ የሚያሳየው ‹‹ ነበርን›› የሚል ብዙ ቁጥር ባንደኛ መደብ ‹‹እኛ›› በሚለው ተገልጿል፡፡ ስለዚህ የባለቤትነትና የግስ ስምምነት በተጨማሪም

የቁጥር ስምምነት አይታይም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ የባለቤትና የግስ እንዲሁም የቁጥር ስመምነትን በግልፅ ካልተረዱ ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ በዖታም አለመስማማት የተነሳ ስህተት በታላሚ ቋንቋ ላይ ባልተሟላ ትምህርት አሰጣጥ የሚመጣ ችግር ለስህተት እንደዳረጋቸው ይገመታል፡፡

ተማሪዎቹ  በክፍል ሶስት በነጻ አስተያየት የተሰጡትን ምላሽ ከተሰጠው ጥያቄ  በምሳሌ ብንወስድ፣ የተራ ቁጥር አንድ ጥያቄ "ድርሰትን ለመፃፍ በምትሞክሩበት ጊዜ ለስህተት የሚያጋልጣችሁን የስህተት አይነቶች ዘርዝሩ::" ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሆሄያት ቅርጽ (አጣጣል)፤ ግድፈት፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፤ ቃላት አጠቃቀም (ድግግሞሽ) እና የአርፍተ ነገር ስምምነት ስህተቶች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተራ ቁጥር 2 በቀረበው ጥያቄ "ድርሰትን ለመፃፍ በምታደርጉት ልምምድ ለስህተት ይዳርጉናል ብላችሁ ያሰባችሁት የስህተት ምንጮች ዘርዝሩ::" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የታላሚውን ቋንቋ ስርአት ሙሉ በሙሉ አለማወቅ፤ የአማርኛ መደበኛ እና ዲቃላ ሆሄያትን በአግባቡ ካለመረዳት፤ መምህራን በጽህፈት ልምምድ ወቅት እገዛ አለማድረግና የተሰጡትን መልመጃዎች ብዙ ጊዜ ተከታትሎ አለማረም እና ግብረ መልስ በአግባቡ ካለመስጠት የተነሳ ስህተቶች እንደሚፈፀሙ ገልዋፀል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ተማሪዎች ለሚፈፅሙት የስህተት አይነቶች በመምህራን መጠይቅ በክፍል 3 በተራ ቁጥር 5 ተማሪዎች ድርሰትን በመፃፍ በሚያደረርጉት ልምምድ ወቅት ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚፈፅሟቸው የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው ተብለው ተጠይቀው ሲመልሱ የሆሄያት ቅርፅ አጣጣል (ግድፈት)ጭመራ የቃላት አጠቃቀም (ድረታ)፤የአረፍተነገር አመሰራረት፤የመስተዋድድ እንድሁም የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የቃላት እጥረትና ትርጉም አለማወቅ ነው በማለት መልሰዋል፡፡

በተራ ቁጥር 6 ተማሪዎች ድርሰትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች መንስኤ (ምንጭ) ናቸው ብለው ያሰቡትን ይዘርዝሩ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እና የፍላጎት ማነስ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም በተዛማች ፅሁፍ በተገለፀው፤ በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች በተጨማሪ ከተማሪዎችና መምህራን የተሰነዘሩት አስተያቶች እንደሚያሳዩት ስተቶቹ

ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ ለተፈፀሙ ስህተቶች ምክንያት ሆነው ከቀረቡት ስህተት ምንጮች መካከል አንዱ የውስጥ ቋንቋ ተፅኖ እንደሆነ ታውቋል፡፡

### 4.3.2. አፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅእኖ

በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በሁለትኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በፅሁፍም ሆነ በንግግር ለመግለፅ ሲሞክሩ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ ተብለው ከቀረቡት ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ አንዱ እንደሆነ በክለሳ ድርሳናቱ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በአፍርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ ከሚያጋጥማቸው ችግር መካከል በድምፅ / በሆሂያት/ ደረጃ፣ በቃላት፣ በሀረግ፣በመስተዋድድ ያለቦታው መግባትና መገደፍ እና በአረፍተነገር አመሰራረት ደረጃ ችግር ታይቷል፡፡ ለምሳሌ፡- በሆሂያት ደረጃ አፋርኛ ቋንቋ አምስት አናባቢዎች እንዳሉት በአንደኛ ክፍል የተማሪዎች የመማሪያ መፃሀፍ በገፅ‹‹8›› ተጠቅሷል፡፡ በነዚህ አናባቢዎች ውስጥ የመጀመሪያው ግእዙ ‹‹ኸ›› ሳድሱ ‹‹እ›› የተባሉት አናባቢዎች የላቸውም፡፡በመሆኑም ‹‹እ›› የተባለችውን ሳድስ አናባቢ በአማረኛ ቋንቋ በሚጠቀምበት ጊዜ ከሳልሱ አናባቢ ‹‹ኢ›› ጋር ያተካኩታል፡፡

ለአብነት ያህልም እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

- ✓ ያ አፋር ብሂረሰብ የሚኖረው በአፋር ‹‹ኪ›› ልል ነው፡፡
- ✓ አፋሮች የራሳቸው ቋንቋ <u>ባሂል</u> እና <u>ወጊ</u> ያላቸው ህዝቦች ናቸው፡፡
- ✓ ያ አፋር ብሂረሰብ ሁለት የ<u>ባህላዊ</u> የጋብቻ አይነቶች አሏቸው፡፡

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት እንደሚቻለው በመጀመሪያው አረፍተነገር ሳድሱን ወደ ሳልስ በመለወጥ ክልል ተብሎ መፃፍ የነበረበት ቃል <u>‹ኪ‹ ልል</u> በማለት ተፅፏል፡፡ ሁለተኛ አረፍተነገር ከመጀመሪያው አረፍተነገር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ‹‹ወግ›› የሚለው ቃል ‹‹ወጊ›› በማለት ሳድሱን ‹‹ግ›› ወደ ሳልስ‹‹ጊ›› ከመቀየሩም በላይ የቃላት ትርጉም እንደቀየረው ያሳያል፡፡በሶስተኛው አረፍተነገር የሚታየው ስህተት ደግሞ ‹‹የ›› የተባለቸው መስተዋድድ ባህላዊ ከሚለው ቃል በፊት ካለቦታዋ በመግባቷ የአረፍተነገሩን ትክክለኛ ተነባቢነት እንድደበዝዝ ሆኗል ፡፡

የአፋርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ግዕዙ ‹‹ኸ›› የሌለው በመሆኑ በቃል መጀመሪያ፣ መሀል እና መጨረሻ ሲመጣ ወደ‹‹አ›› ይለውጡታል፡፡

ለምሳሌ ያአፍር ብሂረሰብ ... መሆን የነበረበት የአፋር ብሂረሰብ ነበር ይህን ሊሆን የቻለው ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ነው፡፡

እነዚህ ከዚህ በላይ በምሳሌነት የቀረቡት የስህተት አይነቶች በምንመለከትበት ወቅት የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ለስህተት መከሰት ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡ መምህራንም ክፍል ሁለት መመሪያ ሁለት ተራ ቁጥር 5 በፅሁፍ ልምምድ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ምን ያህል ነው ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሰጡት ምላሽ 2 (66.66%) ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል ሲሉ 1(33.33%) የሚሆኑት ደግሞ ዝቅተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አንዱ የስህተት ምንጭ እንደሆነ ነው፡፡

### 4.3.3 የማስረፅ ስልት

ይህ የስህተት ምንጭ መንስኤው በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን የሚመለከት ነው።ይህን ሂደትም በፅህፈት ልምምድ ወቅት ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን መጠይቁን ከሞሉት ከ12ኛ ክፍል አፋር ተማሪዎች እና በዚሁ ክፍል በሚየስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መልመጃዎችን መሰረት ያደረገ እና በመማሪያ ቁሳቁስ ዙሪያ በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ሰንጠረዥ 7፡- መልመጃዎችን በሚመለከት ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኝ ምላሽ።**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መምህራን | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 4 | ተማሪዎች ድርሰት ለመጻፍ የሚያግዛቸውን መልመጃዎች ይሰጣሉ? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ እሰጣለሁ። | | |
| | . ብዙ ጊዜ እሰጣለሁ። | 2 | 66.66 |
| | . አልፎ አልፎ እሰጣለሁ። | 1 | 33.33 |
| | . በሁለት ወር አንድ ጊዜ እሰጣለሁ | | |
| 5 | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ፅሁፋዊ መልመጃዎች ሰርተው ይመጣሉ? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ | 2 | 66.66 |
| | . ብዙ ጊዜ ይሰራሉ። | | |
| | . አልፎ አልፎ ይሰራሉ። | 1 | 33.33 |
| | . አብዛኛውን ጊዜ አይሰሩም። | | |
| 6 | ተማሪዎቹ የሰሩትን መልመጃዎች በወቅቱ አርመው ይመልሳሉ? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ | 1 | 33.33 |
| | . ብዙ ጊዜ | | |
| | . አልፎ አልፎ | 2 | 66.66 |
| | . አብዛኛውን ጊዜ አላርምም፡፡ | | |

### ሰንጠረዥ 8፡- መልመጃዎችን በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ተማሪዎች | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ድርሰት እንድትፅፉ (እንድትለማመዱ) መልመጃዎችን ይሰጧችኋል? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣሉ። | 15 | 13.6 |
| | . ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ። | 63 | 57.3 |
| | . አልፎ አልፎ ይሰጣሉ። | 24 | 21.8 |
| | . በሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰጣሉ። | 8 | 7.3 |
| 5 | መምህራችሁ የሰጡትን መልመጃዎች ትሰራለህ/ትሰሪለሽ? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ እሰራለሁ፡፡ | 6 | 5.5 |
| | . አልፎ አልፎ እሰራለሁ፡፡ | 72 | 65.5 |
| | . ከሁለት ወር አንድ ጊዜ እሰራለሁ፡፡ | 7 | |
| | . ብዙ ጊዜ አልሰራም፡፡ | 25 | 22.7 |
| 6 | መምህራችሁ የሰጡትን የድርሰት መልመጃ ለእያንዳንዱን ተማሪ አርመው ይመልሳሉ? | | |
| | . አብዛኛውን ጊዜ አርመው ይመልሳሉ | 20 | 18.20 |
| | . ብዙ ጊዜ አርመው ይመልሳሉ | 15 | 13.6 |
| | . አልፎ አልፎ አርመው ይመልሳሉ | 70 | 63.6 |
| | . አብዛኛውን ጊዜ አርመው አይምሱም | 5 | 4.55 |

በሰንጠረዥ 7 እና 8 በቀረበው መሰረት መልመጃዎችን በሚመለከት ከተማሪዎች እና ከመምህራን ፅሁፋዊ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኖ ለማቅረብ ተሞክሯል። በዚህ መሰረት በተማሪዎች መጠይቅ ክፍል ሁለት መመሪያ 1 ቁጥር 4 ላይ መምህራችሁ ድርሰት እንድትፅፉ (እንድትለማመዱ)መልመጃዎችን ይሰጧችኋል? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል 15 (13.6%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ ይሰጡናል ሲሉ 63(57.3%) ብዙጊዜ ይሰጡናል ሲሉ 24(21.8%) አልፎአልፎ ይሰጡናል ብለዋል፡፡ እንዲሁም 8 (7.8%) የሚሆኑት ደግሞ ከሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰጠናል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ከላይ ከተዘረዘሩት መመዘኛዎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ይሰጡናል የሚሉት ተማሪዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል። በመመምህራን መጠይቅ በተራ ቁጥር 4 ላይ ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የሚያግዛቸው ልምምድ እንዲያደርጉ መልመጃዎች ይሰጣሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 2 (6.66%) የሚሆኑት መምህራን ብዙ ጊዜ እሰጣለሁ

ሲሉ 1 (33.33) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚሰጡ ገልፀዋል።በዚህ መሰረት ብዙ ጊዜ እሰጣለሁ የሚሉ መምህራን ቁጥር ከፍተኛ ነው።

በዚህ መጠየቅ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራን ተመሳሳይ ምላሽ የሰጡ ቢሆንም በተማሪዎች መጠይቅ መመሪያ 2 ቁጥር 6 ተማሪዎች ድርሰት በመለማመድ ረገድ መምህራን እገዛ ያደርጋሉ?በሚለው ጥየቄ በተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ ዝቅተኛ (አነስተኛ) እገዛ እንደሚያደርጉ ተገልፀዋል።በመሆኑም መምህራን ብዙ መልመጃዎችን ቢሰጡም ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ አስፈላጊውን ክትትል እንደማያደርጉ ያመለክታል።በቁጥር 5 የቀረበው ጥያቄ መምህራችሁ የሰጡትን መልመጃዎች ትሰራለህ (ትሰሪያለሽ)? የሚል እንድምታ ነበርው። በዚህ መሰረት መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል አብዛኛውን ጊዜ እሰራለሁ የሚሉ ተማሪዎች ቁጥር 6(5.5%) ፣አልፎ አልፎ እሰራለሁ 72(65.5%)፣ ብዙጊዜ አልሰራም የሚሉት ደግሞ 25(22.7%) ናቸው።በተራ ቁጥር 5 በተመሳሳይ ለመምህራን የቀረበው ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ፅሁፋዊ መልመጃዎች ሰርተው ይመጣሉ? የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ አንድ መምህርት ወይም 33.33% አልፎ አልፎ ይሰራሉ ሲሉ 2(66.66%) የሚሆኑት መምህራን ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰሩ ገልፀዋል።

በዚህ መጠይቅ አልፎ አልፎ እንሰራለን የሚሉ ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ሲሆን መምህራን ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ ያሉት ካሉት መምህራን መካከል ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል።ስለዚህ በሁለት አካላት የተሰጡት ምላሾች የሀሳብ መጣረስ ይታያል።በመሆኑም በተማሪዎቹ መጠይቅ በመመሪያ 3 በተራ ቁጥር 6 ድርሰትን በመለማመድ ረገድ መምህራን ለተማሪዎቻቸው እገዛ ያደርጋሉ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ አነስተኛ (ዝቅተኛ) እገዛ እንደሚያደርጉ ብዙዎቹ ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተዋል።
በዚህ መሰረት መምህራን የሰጡትን መልመጃዎች አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ ቢሉም መልመጃዎቹን እንዲሰሩ እዚህ ግባ የሚባል እገዛ ስለማያደርጉ ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን መልመጃዎች አልፎ አልፎ እንደሚሰሩ ያስገነዝበናል።

በተራ ቁጥር 6 ለተማሪዎቹ የቀረቡ ጥያቄ መምህራችሁ የሰጡትን መልመጃዎች አርመው ይመልሳሉ?የሚል ሲሆን መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል አብዛኛውን ጊዜ አርመው ይመልሳሉ የሚሉት 20 (18.20%) ፣ ብዙ ጊዜ አርመው ይመልሳሉ 15 (13.6%)፣አልፎ

አልፎ አርመው ይመልሳሉ 70 (63.6%) ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ አይመልሱም የሚሉት ደግሞ 5 (4.55%) ናቸው።ስለዚህ ከተሰጡት መመዘኛዎች መካከል አልፎ አልፎ አርመው ይመልሳሉ የሚሉ ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል።መምህራንም በተመሳሳይ ለተማሪዎች የሰጡትን መልመጃ በወቅቱ አርመው ይመልሳሉ? በማለት ለተጠየቁት ጥያቄ 2 (66.66%) የሚሆኑት መምህራን አልፎ አልፎ እንደሚያርሙ የገለፁ ሲሆን 1 (33.33%) ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያርሙ ገልፀዋል።

ይሁን እንጂ መምህራን ብዙ ጊዜ የማያርሙ ከሆነ ለዚህም በምክያትነት ያስቀመጡት በመምህራን መጠይቅ ክፍል ሶስት መመሪያ ሶስት በተራ ቁጥር 3 እርስዎ የተማሪዎችን መልመጃዎች ሲያርሙ የገጠመዎት ችግር ካለ ይግለጹ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ብዙዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያትን ለይተው ባለማወቃቸው የተነሳ የሚመሰርቱትን ቃላትም ሆነ አረፍተነገር የሆሄያት ግድፈት፣ ጭመራ፣ የቃላት አለቦታው መግባት ወዘተ ተዳምሮ የፃፉት ፅሁፍ ግልጽ ስላልሆነ በተጨማሪም ለቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን ብዙ ጊዜ እንዳላርም አድርጎኛል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በክፍል ሶስት መመሪያ ሶስት ተራ ቁጥር 4 ላይ ተማሪዎች ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው የስህተት አይነቶች ምን ምን ናቸው? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከሰጧቸው መልሶች መካከል የሆሄያት ግድፈት እና ሀሳብን የመግለፅ ችግር እንደሆነ ገልፀዋል።በተጨማሪም በተራ ቁጥር 13 አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ በቋንቋው በቀላሉ ማንበብ እና መፃፍ ሊሳካላቸው የማይችሉበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 66.66% የሚሆኑት መመህራን የመደበኛ እና ዲቃላ ሆሄያትን በቀላሉ አለመለየት አንዱ ለስህተት መፈጠር አንዱ ችግር እንደሆነ ገልፀዋል።

ሰንጠረዥ 9፡- **በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎችን የሚመለከት የመምህራን መጠይቅ ምላሽ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መምህራን | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 14 | የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ ተማሪዎች ፅህፈትን በተሻለ ሁኔታ እንዲለማመዱ የሚያደርጓቸው መልለጃዎች የትኞቹ ናቸው? | | |
| | . ክፍል-1 | | |
| | . ክፍል-2 | 3 | 100 |
| | . ክፍል-3 | | |
| | . ክፍል-4 | | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ፅህፈትን በተሻለ ሁኔታ እንዲለማመዱ የሚያደርጓቸው መልመጃዎች ክፍል ሁለት እንደሆነ ሁሉም መምህራን ገልፀዋል።

**ሰንጠረዥ 10፡- በመማሪ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ መልመጃዎችን የሚመለከት የተማሪዎችና የመምህራን መጠይቅ ምላሽ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | መመዘኛዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 7 | አሁን በምትማሩበት የ12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች ፅህፈትን በማለማመድ በኩል ምን ያህል ጠቀሜታ አላቸው? | ተማሪዎች | | | 25 | 22.7 | 75 | 68.2 | 10 | 9 |
| 4 | አሁን በምታስተምርበት የ12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች ፅህፈትን በማለማመድ በኩል ምን ያህል ጠቀሜታ አላቸው? | መምህራን | | | | | 2 | 66.66 | 1 | 33.33 |

ከሰንጠረዥገዙ መረዳት እንደሚቻለው አሁን በምታስተምርበት (በምትማሩበት) የ12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች ፅህፈትን በማለማመድ በኩል ምን ያህል ጠቀሜታዎች አሏቸው።ለተባለው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከፍተኛ ያሉ 25 (22.7%) መካከለኛ ያሉ 75 (68.2%) ዝቅተኛ ያሉ ደግሞ 10 (9%) ሲሆኑ የመፅሀፉን ጠቀሜታ በተመለከተ መካከለኛ ወይም የተሻለ ጠቀሜታ አለው ያሉ ተማሪዎች 75 (68.2%) በመሸፈን ትልቁን ድርሻ ይዘዋል።

መምህራን ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 1 (33.33%) ዝቅተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ሲገልፁ 2 (66.66%) የሆኑት ደግሞ መካከለኛ ጥቅም እንዳለው ገልፀዋል።

በክፍል 3 በጥያቄ 2 አሁን የምታስተምሩበት መፅሀፍ የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማሻሻል ፋይዳው ምን ያህል እንደሆነ ቢያብራሩልኝ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ መፅሀፉ በተወሰነ ወይም መካከለኛ በሚባል ደረጃ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ አናሳ መሆን እና ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን በማስተማር ሂደቱ ላይ ችግር ፈጥሯል።

### 4.3.4. ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች

ይህ የስህተት ምንጭ ቀደም ሲል ከተዘረዘሩት የስህተት ምንጮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ ነው ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ከመማሪያ ክፍል ውጭ በአካባቢያቸው ስለሚታዩትና ስለሚፈጠሩት መልካምም ሆነ መጥፎ ገጠመኝ እንድሁም ስለራሳቸውና ስለቤተሰባቸው ሁኔታ በአዕምሮአቸው ውስጥ ይዘውት የመጡትን ጉዳይ በማሰላሰል በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርት እንደማይከታተሉ ተፅኖ እንደሚያሳድርባቸው (ደብሬ 1990፡110) ኖሪሽ(1990፡19)ን በመጥቀስ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በተጨማሪም በተማሪዎች መጠይቅ ክፍል ሶስት ተራ ቁጥር 4 አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋችሁ እንደመሆኑ መጠን የአማርኛ የፅህፈት ትምህርት በተመለከተ የሚኖርህ/ሽ/አዎንታዊ እና አሉታዊ አመለካከት አብራራ/አብራሪ/ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የአማርኛን ቋንቋ ንግግርም ሆነ ፅህፈት መማር ጥሩ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት ግን አብዛኛው የአካባቢያችን ኗሪ ለቋንቋው የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ በተጨማሪም ቋንቋውን ተምረው በአካባቢያቸው ስራ ለመቀጠርም ሆነ ፈተና ላይ ለመቅረብ በአፋረኛ ቋንቋ የሚሰጥ በመሆኑ ቋንቋውን መማር እንብዛም ጠቀሜታ የሌለው መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡በመምህራን መጠይቅ መመሪያ ሁለት ቁጥር 1 በአፋረኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ፅኅፈት ክሂልን ሲማሩ ያላችሁ ፍላጎት ምን ያህል ነው ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 2/66.66%/የሚሆኑት መምህራን ዝቅተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ ጫና ከማሳደሩም ባሻገር በድርሰታቸው ውስጥ ስህተት እንዲፈጽሙ ምክንያት ሆኗል፡፡

ስህተት መፍጠር እንደ አላስፈላጊ ክስተት እና እንደነውር የሚታይ ሳይሆን በመማር ማስተማር ውስጥ የትምህርቱ አንድ አካል ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚገባ Richards (1974፡23) ገልጸዋል፡፡ ሌሎችም ለመማር ካለ ፍላጎት መቀስቀስ ጋር ያገናኙታል፡፡ ይህ ፅህፈትን ለማስተማር የቀረበው ነገር ምናልባት ከተማሪው ፍላጎት ጋር የመጣ ችግር ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ፡፡

በመሆኑም ከመምህራንና ከተማሪዎች የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልም ለመማር ተጠኝ ተማሪዎች ያላቸው

ፍላጎት ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ አብዘኛዎቹ ተማሪዎች ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ (አነስተኛ) እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ከቀረቡት መካከል ተማሪዎቹ ድረሰትን ለመፃፍ በሚያደርጉት ልምምድ የመምህራን እገዛ ማነስ፣ መምህራን መልመጃዎችን አብዘኛውን ጊዜ አለማረም፣ ትምህርቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚሰጠው የ12 ክፍል የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና አለመስጠቱ፣በአሁኑ ሰአት ማህበረሰቡ ለቋንቋው የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ መሆን፣ ተማሪዎች ቋንቋውን ምን ይጠቅመኛል የሚል ስሜት መኖር በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት አሳድሮባቸዋል ፡፡ በዚህ የተነሳ ስነልቦናዊ ሁኔታዎች የስህተት ምንጭ ሆነዋል፡፡

### 4.3.5. ድምጸ ልሳናት

ይህ የስህተት ምንጭ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች መካከል አንዱ ነው፡፡ የስህተቱ መንስኤ የአማርኛ ቋንቋ ድምፅ ልሳናት ቅርፅ (አጣጣል) በትክክል ካለመረዳት የተነሳ የሚከሰት ስህተት እንደሆነ በክለሳ ድርሳናቱ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

ይህን ጥናት ለማረጋገጥ መጠይቁን የሞሉትን የ12ኛ ክፍል አፋር ተማሪዎች እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅሁፍ መጠይቆቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ 11፡- **ድምፅ ልሳናትን በሚመለከት ከተማሪዎቹ ፅሁፍአዊ መጠየቅ የተገኘ ምላሽ**

| ተራ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | |
|---|---|---|---|
| | | ዛት(መጠን) | % |
| 8 | መምህራችሁ መልመጃዎችን የሚሰጡ ከሆነ የትኞቹ የስህተት አይነቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ? | | |
| | - የሆሄያት ቅርፅ(አጣጣል) ላይ | 40 | 36.4 |
| | - የቃላት አመራረጥ ላይ | 21 | 19.0 |
| | - የአረፍተነገር አመሰራረት ላይ | 17 | 15.5 |
| | - የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | 32 | 29.0 |
| | - ከዚህ የተለየ ካለ | | |
| 11 | በፅህፈት ልምምድ ወቅት ለስህተት መፈጠር መንሰኤ ይሆናሉ ብለህ/ሽ/ያሰብከው/ሽው/ ነጥብ የትኛው ነው? | | |
| | - የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ድክመት | 10 | 9.0 |
| | - የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያት ብዛትና ቅርፅ (አጣጣል) | 65 | 59.0 |
| | - የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት | 20 | 18.2 |
| | - የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው ስርዓት | 15 | 13.7 |

ሰንጠረዥ 12፡- ድምጸ ልሳናትን በሚመለከት ከመምህራን ፅሁፋዊ መጠየቅ የተገኘ ምላሽ

| ተራ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት(መጠን) | % |
| 8 | መልመጃዎችን የሚያርሙ ከሆነ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈፅሙት ስህተት የትኛው ነው? | | |
| | - በሆሄያት ቅርፅ ላይ | 2 | 66.6 |
| | - በቃላት አመራረጥ ላይ | | |
| | - በአረፍተነገር አመሰራረት ላይ | | |
| | - በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ | 1 | 33.33 |
| 9 | ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ስህተት የሚፈፅሙ ከሆነ ለስህተታቸው ምክንያት ይሆናሉ ብለው ከገመቷቸው ጉዳዩች መካከል ቀደሚው የትኛው ነው ብለው ያስባሉ? | | |
| | - የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ድክመት | | |
| | - የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ | 1 | 33.33 |
| | - የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያት ቅርፅና ብዛት (አጣጣል) | 2 | 66.66 |
| | - የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው ስርዓት አስቸጋሪነት | | |
| | - የተለየ ካለ በፅሁፍ ይግለፁ | | |

በሰንጠረዥ 11 እና 12 በቀረበው ድምፅ ልሳናትን በሚመለከት ከተማሪዎችና ከመምህራን ፅሁፋዊ መጠየቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትነው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረት በተማሪዎቹ መጠየቅ ክፍል ሁለት መመሪያ አንድ ተራ ቁጥር "8" መምህራችሁ መልመጃዎችን የሚያርሙ ከሆነ የትኞቹ የስህተት አይነቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 40(36.4%) የሚሆኑት ተማሪዎች የሆሄያት ቅርፅ (አጣጣል) ላይ ፣ 21(19%) የቃላት አመራረጥ ፣17(15.5%) በአረፍተነገር አመሰራረት ያሉ ሲሆን 32(29%) ደግሞ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ መሰረት በሆሄያት ቅርፅ (አጣጣል) ላይ ያተኩራሉ የሚሉት ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡

በተመሳሳይ በመምህራን መጠየቅ ቁጥር "8" መልመጃዎችን የሚያርሙ ከሆነ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈፀሙት ስህተት የትኛው ነው? ተብሎ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ 2/66.66%/ የሚሆኑት መምህራን በሆሄያት ቅርፅ ላይ ያሉ ሲሆን 1/33.33%/ ደግሞ በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው መምህራኑ በሆሄያት ቅርጽ ላይ በሚል የሰጡት ምላሽ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከመረጃው ለመረዳት የተቻለው ለተማሪዎቹ ስህተት መፈፀም ምክንያት የሆሄያት ቅርፅ (አጣጣል) ለይቶ አለማወቅ ችግር በጽህፈት ልምምድ ጊዜ ለስህተት እንደሚያጋልጣቸው ተማሪዎች ሆነ መምህራን ተመሳሳይ ምላሽ የሰጡ መሆኑን ነው፡፡

በተማሪዎች መጠይቅ ተራ ቁጥር "11" በጽህፈት ልምምድ ወቅት ለስህተት መከሰት መንስኤ ይሆናሉ ብለህ/ሽ/ያሰብከው/ሽው/ ነጥብ የትኛው ነው ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያት ቅርፅ (አጣጣል) በማለት 65/59%/ የሚሆኑት ተማሪዎች የመለሱ ሲሆን በተመሳሳይ በተራ ቁጥር "9" ተማሪዎች ድርሰት ሲፃፍ ስህተት የሚፈፅሙ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው የትኛው ነው ብለው ያስባሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራኑ የሰጡት ምላሽ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ 1/33.33%/ እና የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያት 2/66.66%/ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በተማሪዎች መጠየቅ ክፍል ሶስት ነፃ አስተያየት ምላሽ በተራ ቁጥር "1" ድርሰትን ለመፃፍ በምትሙክሩበት ጊዜ ለስህተት የሚያጋልጡህ/ሽ/ የስህተት አይነቶች ዘርዝር/ዘርዝሪ/? ተብለው ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 68% የሚሆኑት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመደበኛ እና የዲቃላ ሆሄያት አለመለየት ያሉ ሲሆን 20% የሚሆኑት ደግሞ የቃላት እጥረት ሲሉ ሌሎች 32% የሚሆኑት ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እንደሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በመመህራን መጠየቅ በክፍል ሶስት መመሪያ ሶስት በነፃ አስተያየት ምላሽ ተራ ቁጥር "6" ተማሪዎች ድርሰት በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ /መንሰኤ/ ናቸው ብለው ያሰቡትን ይዘርዝሩ? ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 33.33% የሚሆኑት አፍ -የፈቱበት ቋንቋ ሲሉ 66.66% ዎቹ ደግሞ የአማርኛ ሆሄያት በአንደኛ ደረጃ እያሉ በትክክል ባለመለየታቸው አሁን ባሉበት የክፍል ደረጀ ድርሰት ሲፃፍ በቃላት

ግንባታና በአረፍተነገር አመሰራረት ላይ ሀሳባቸውን በአግባቡ ለመግለፅ በመቸገር ስህተት እንደሚፈፅሙ ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከተማሪዎች እና ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ መረዳት የተቻለው ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ስህተት እንደሚፈፅሙ የስህተት ምንጭ የሆኑት በዋናነት የታላሚው ቋንቋ ድምፅ ልሳናት /ቅርፅ/አጣጣል/ ለይቶ አለማወቅ ቃላትንም ሆነ አረፍተነገርን ለመመስረት አስቸጋሪ በመሆኑ ለስህተት መከሰት ምክንያት እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

## 4.4. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአፍርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ከጽሁፎቻቸው ውስጥ ስህተቶችንና የስህተት ምንጮችን ነቅሶ በማውጣት የስህተት ትንተና ዘዴን ተጠቅሞ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ነው፡፡

ይህንን አላማ ለማሳካት ያስችላሉ የተባሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን በመመለስ የጥናቱ ውጤት ላይ ተደርሷል፡፡

1. የአማርኛ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንምን ናቸው?
2. የስህተቶቹ የድግግሞሽ መጠንስ ምን ያህል ነው?
3. ለስህተቶቹ መከሰት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉት የስህተት ምንቸጮች እነማን ናቸው?

ከላይ የተጠቀሱትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ተጠኚ ተማሪዎችን ድረሰት በማፃፍ፣ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጹሁፍ መጠየቅ በማሰሞላት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን የሚከተሉት ሊሚቶች ላይ ተደርሷል፡፡

በጥናቱ ወጤት መሰረት በአማርኛ ኢ-አፍፈት ተጠኚ ተማሪዎች በሁለት ተከታታይ ዙር የጻፏቸው 220 ድርሰቶች ሲሆኑ አንድ ድርሰትም በአማካይ 80.17 ቃላት ተጽፎ ይገኛል፡፡ በ17637 ቃላት ውስጥ የፈጸሟቸው አጠቃላይ ስህተቶች 3526 እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡በአንድ ድርሰትም ውስጥ የተቆጠሩትአማካይ ስህተቶች 16.02 ሲሆኑ በ100 ቃላት ወስጥ የተጻፈ አንድ ድርሰት በውስጡ ያለው የስህተት ድግግሞሽ መጠን 19.98 መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዚህ ጥናት ተጠኚ ተማሪዎች በጻፉችው ድርሰቶች ወስጥ የፈጸሟቸው ስህተቶች በአራት ዋና ምድብ ተከፋፍለው ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም የቋንቋ አጠቃቀም ፣የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣የቋንቋ አውቃቀርና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት አበይት የስህተት ምድብ አየነቶች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ ይህም 1803 የሚሆኑ ስህተቶችን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህ በመቶኛ ሲሰላ 51.13% ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ 8.2፣የስሁተት ድግግሞሹ ደግሞ 10.23 እንደሆነ ተችሏል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የሆሄያት ቅርጽ (አጣጣል) ባለማወቃቸው የተነሳ ሆሄያትን ቀያይሮ የመጻፍ፣ አላስፈላጊ የሆኑ ሆሄያትን በቃላት ላይ የመጨመርና የመግደፍ ስህተቶች እንደታዩ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

በድርሰቶቹ ውስጥ ከታዩት አጠቃላይ አበይት የስህተት ምድቦች ውስጥ በቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ሆኖ ተገኘቷል፡፡ በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተገኘው የስህተት መጠን 1034 ሲሆን የመቶኛ ሲሌቱ ደገሞ 29.33% ነው፡፡ አማካይ የስህተት መጠኑ 4.7 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 5.86 ሆኖ ተገኘቷል፡፡ ይህ የስህተት ምድብ በስሩ አራት ነጥብ፣ድርብ ሰረዝ፣ነጠላ ሰረዝ፣ይዘትና ቅንፍ የመሳሰሉ ንኡሳን ስህተቶችን በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ እንደተፈጸሙ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ስርአተ ነጥቦች ሀሳብን ስሜትን ወዘተ በጥቅሉ መልዕክትን ከጸሀፊው ለአንባቢው ወይም ለአድማጩ ግልጽና ትክክለና በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ነው።ይሁን እንጅ መልዕክትን ግልጽና ግብ መቺ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ በሚዋቀረው አረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ የሆነውን የነጥብ ስርአት በተገቢ አግባቡ አለመጠቀም ችግር ተጠኝ ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈጽመ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ከታዩት አበይት የስህተት ምድቦች መካከል በስህተት ብዛቱ በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው።ይህ የስህተት ምድብ 577የሚሆኑ ስህተቶችን ይዞ ይገኛል። ይህ ቁጥር በመቶኛ ሲቀመጥ 16.36% ነው። አማካይ የስህተት መጠኑም 2.62 ሆኗል። በመቶ ቃላት ውስጥ ያለው የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 3.27 መሆኑ ተረጋግጧል።

በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የቃላት አጠቃቀም፣አረፍተ ነገር ስምምነት ፣የመስተዋደድ አፈባብ፣ የጾታ ፣የመደብና የቁጥር የሚባሉት ንዑሳን ስህተቶች ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸሙ ሲሆን በአረፍተ ነገር ስምምነት ወቅት ቃላትን ተገቢ በሆነ ቦታ አለመጠቀም፣ የባለቤትና የግስ አለመስማማት፣ የአረፍተ ነገር መፋለስ ችእንደተፈጸመ የጥናት ውጤት ያሳያል።

በዚህ ጥናት አበይት የስህተት ምድቦች ውስጥ የመጨረሻውን ደረጃ የያው መለየት ያልተቻሉ የስህተት ምድብ ነው። ይህ ምድብ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በቀላሉ ስህተቶችን ለይቶ ለማውጣት በማያስችል ሁኔታ ተዘባራርቀው የተቀመጡ፣አረፍተ ነገሮቹ መቋጫ የሌላቸውና ውስብስብ ያሉ የቃላት ስብስብ በመሆናቸው የተፈጸመ ስህተቶችን መለየትና ግብረመልስ መስጠት አለመቻሉን መገንዘብ ተችሏል። በዚህ ምድብ ውስጥ የተገኙት ስህተቶች 112 ሲሆኑ በመቶኛ ሲሰላ 3.18% ነው። አማካይ የስህተት ብዛቱም 0.51 ሆኗል።የስህተት ድግግሞሽ መጠን ደግሞ 0.64 መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

የማስረጽ ስልትን በተመለከተ በዚህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው ሶስተኛውን መሰረታዊ የጥያቄ ለመመለስ በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰቶች ከተፈጸሙ ስህተቶች ትንተና፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆች ምላሽ መረጃዎች ተገናዝበው በመውሰድ በዋናነት የታዩት የስህተት ምንጮች ውስጠቋንቋ ተጽዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የማስረጽ ስልት ተጽዕኖ፣ስነልቦናዊ ሁኔታዎችና የአማርኛ ቋንቋ ድምጸ ልሳናት እንደሁኑ የጥናቱ ውጢኣት ያሳያል።

በዚህ ጥናት መረጃ መሰረት የቋንቋ ትምህርቱን ለማስተማር የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉት የመልመጃ ይዘቶች ጽህፈትን በማለማመድ በኩል ያላቸው ድርሻ 68.2% የሚሆኑ ተማሪዎችና 66.66% የሚሆኑት መምህራን በተወሰነ ደረጃ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ቢገልጹም ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ ዝቅተኛ መሆኑ አብዛኛዎቹ ተማሪዎችና መምህራን ገልጸዋል። በዚህ መሰረት በክፍል ደረጃው ከቀረበው የትምህርት ይዘትጋር የማይመጣጠን መሆኑ መምህራን ተገቢ በሆነ መልኩ ተማሪዎቹን እውቀት ለማስጨበጥ፣መልመጃዎችን ለማረም፣ በአጠቃላይ በቂ የሆነ እገዛ ለማድረግ እንዳልቻሉ የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ በዚህ የስህተት ምንጭ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናቱ 2.4.4 እንደተገለጸው ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አተያይና የመማር ፍላጎት እንድሁም ውስጣዊ ተነሳሽነት ያለመኖር ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

ከተማሪዎቹ መጠየቅ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው የአማርኛ ቋንቋን ንግግርማ ሆነ ጽህፈትን መማር ጥሩ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ማህበረሰቡ ለቋንቋው የሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት ፣በ12ኛ ክፍል የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናላይ አለመሰጠቱ እና ስራ ለመቀቀጠርም ሆነ ለመወዳደር ቋንቋው ግልጋሎት አለመስጠቱ የመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮባቸውል። በዚህ የተነሳ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በፍላጎት ሳይሆን በግደለሽነት የሚማሩ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

ድምጸ ልሳናትን በተመለከተ በዚህ ጥናት መረጃ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ ድምጸ ልሳናትን ቅርጽ(አጣጣል) በትክክል ካለመረዳትና ካለመለየታቸው የተነሳ የሚከሰቱ ስህተቶች እንደሆኑ በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ተገልጿል። በተጨማሪም ከተማሪዎቹ ድርሰት፣ ከተማሪዎቹና ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽመገንዘብ እንደተቻለው ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የአማርኛ ሆሄያትን በአንደና ደረጃ እያሉ በትክክል ባለመለየታቸው የተነሳ ስህተቶቹ አሁን ባሉበት የክፍል ደረጃ ላይ በመድረስ በቃላትና በአረፍተ ነገር አመሰራረት ላይ ተጽዕኖ በማሳደር በሚጽፉት ድርሰትም ሆነ ሌሎች መልመጃዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደሩ ዋነኛ የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደቻለ የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖን በተመለከተ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋቸውን አድስ ስርአት ከለመዱ በኋላ ህጉን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል በመረዳት ለመናገርና ለመጻፍ በሚያደርጉት ሙከራ የተፈጸመ ስህተት እንደሆነ በክለሳ ድርሳናቱ ተገልጿል።ስህተቶቹም በቋንቋ  አጠቃቀም የስህተት አይነት ምድብ ስር ካሉት ንዑሳን ስህተቶች መካከል ባልተሟላ ትምህርት አሰጣጥ የተነሳ የሆሄያት ቅርጽ(አጣጣል) ባለመለየት ምክኒያት አላገባብ እንደተጠቀሙ አብዛኛዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ይህ ስህተት እንደታየ የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በጽሁፍም ሆነ በንግግር ለመግለጽ ሲሞክሩ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጭ እንደሆነ በክለሳ ድርሳናቱ ተገልጿል። በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ

ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል በሆሄያት ደረጃ፣ በቃላት፣ በሀረግና በመስተዋድድ ያለቦታቸው መግባትና መግደፍ እንድሁም በአርፍተ ነገር አመሰራረት ደረጃ ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ስህተቶችን ለማየት ተችሏል። በመምህራን መጠይቅም በጽሁፍ ልምምድ ወቅት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ እንዳለው የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሐሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

አለም አሁን በደረሰበት የስልጣኔ ደረጃ የሰው ልጅ በሳታላይት አማካይነት መልዕክት ማስተላለፍና መቀበል ቢችልም ሀሳቡን በሚታይና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ የፅህፈት ክሂል እንደሚያስፈልገው ይታመናል። ይሁን እንጅ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ለኢ-አፍፊት ተማሪዎች በተለይ የመፃፍ ክሂልን አጥኚው ሲያስተምሩ የተለያዩ ተግዳሮቶች የገጠሙት በመሆኑ ጥናት እንድካሄድ እንዳነሳሳው በምዕራፍ አንድ ተገልፃል።

በመሆኑም ይህ ጥናት በአፋር ክልል በሚገኙ የዱብቲና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ሲሆን የጥናቱ ተተኳሪዎችም በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

ጥናቱም ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል ተብሎ የታሰበ ነው።

እነዚህም፦

1. የአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?
2. የስህተቶቹ የድግግሞሽ መጠንስ ምን ያህል ነው?
3. ለስህተቶቹ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት የስህተት ምንጮች እነማን ናቸው? የሚሉት ሲሆኑ ጥናቱ ለነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልሶች ለመስጠት እንዲችል በመጀመሪያ ተጠኚዎቹ እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል።

አስፈላጊውን መረጃዎች ለማግኘት በአንድ በኩል ተጠኚዎቹ ተማሪዎች ድርሰት ፅፈዋል። በሌላ በኩል ተጠኚዎች ተማሪዎችና መምህራን መጠይቆቹን እንዲሞሉ ተደርጓል።

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በመጀመሪያ በድርሰትና በመጠይቅ አማካይነት ከተሰበሰቡ በኋላ በስህተት ትንተና የአጠናን ዘዴ አማካይነት ስህተቶች በአይነት

ተለይተውና ተቆጥረው ተተንትነዋል። በትንተናው በተገኘው ውጤት መሰረት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ተመልሰዋል።

በጥናቱ ውጤት መሰረት ተማሪዎች በማርኛ ቋንቋ ሁለት ጊዜ በጻፏቸው 220 ድርሰቶች ውስጥ 3526 ስህተቶች ተገኝተዋል። አማካይ ስህተቱም 16.03 ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ የሚገኘው የስህተት ድግግሞሽ 19.99 መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የተተኮረባቸው ስህተቶች በአራት ምድብ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እነሱም የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው። ከአራቱ የስህተት ምድቦች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሸፈነው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት 1803 (51.13%) ነው። ይህ አብይ የስህተት ምድብ የሆሄያት ቅርፅ፣ የሆሄያት ግድፈት፣ የቃላት ድግግሞሽ (ድረታ) እና የሆሄያት ጭመራ (እከላ) አጠቃቀም ስህተቶችን አካቶ ይዟል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ከተገኙት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን ይህም 1034(29.33%) የሚሆነውን ቁጥር ሸፍኖ ይገኛል። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተገኘው አማካይ የስህተት መጠን 4.7 ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ መጠን 5.86 ነው። በዚህ የስህተት ምድብ አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝ፣ ቅንፍ እና አንድ ነጥብ(ይዘት) አጠቃሎ በስሩ ይዞ ይገኛል። በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የታዩት ስህተቶች አራት ነጥብን በ/አንድ ነጥብ /፣ነጠላ ሰረዙን በሁለት ነጥብ በመተካት ስርአተ-ነጥብን ያለ አግባብ በመጠቀም የሚፈፀሙ ስህተቶች እንደሆኑ ተረጋግጧል።

በድርሰቶቹ ውስጥ ከተገኙት አጠቃላይ ስህተቶች ሶስተኛ ደረጃን የያዘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ 577/16.36%/ስህተቶች ተገኝተዋል። አማካይ የስህተት መጠኑ 2.62 ሲሆን አማካይ ድግግሞሽ ደግሞ 3.22 ነው። በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የተካተቱ የአረፍተነገር ስምምነት፣ የቃላት ድግግሞሽ ፣እና የመስተዋድድ አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው። በመስተዋድድ ደረጃ የተፈፀሙት ስህተቶች መግደፍ፡ መተካትና አለቦታቸው መግባትን ያመለክታል።

በአራተኛ ደረጃ የተቀመጠው የስህተት አይነት ምድብ መለየት ያልተቻሉ ስህተቶችን የሚመለከት ነው። የስህተት ብዛቱም 112 /3.18%/ ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ 0.51 ይሆናል።ይህ የስህተት ምድብ እንደሌሎች ምድቦች ንኡሳን የስህተት አይነቶች የሉትም።

በጥናቱ አላማ መሰረት በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ተብለው የተገመቱት የውስጥ ቋንቋ ተፅዕኖ፣የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስረፅ ስልት፣ ስነልቦናዊ ሁኔታዎችና ድምጸ ልሳናት ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የስህተት ምንጮች ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ፡በመምህራንና በተማሪዎች የተሞሉ መጠይቆች ጥቅም ላይ ውለል።

በአማርኛ ቋንቋ ውስጣዊ ተፅዕኖ የተነሳ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለስህተት ሊጋለጡ እንደሚችሉ ተስተውሏል። ለስህተት የተጋለጡባቸው ምክንያቶች ያልተሟላ ትምህርት፣ የቃላት ድግግሞሽ እና የተሳሳተ ማጠቃለያ እንደሆኑ ተጠቅሰዋል። በድምፅ /በሆሄያት/ አጠቃቀም ዙሪያ ከተከሰቱት ስህተቶች መካከል ሆሄያትን አላግባብ በመጠቀም የሚፈጸሙ ስህተቶች ይገኙበታል። እነዚህ ስህተቶች በተሳሳተ ማጠቃለያ ምክንያት የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው፡፡

የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ በድምጽ፡ በቃላት፣በሀረግና በአረፍተነገር ዙሪያ ለሚከሰቱ ችግርና ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ማወቅ ተችሏል።

በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ለስህተት ምንጭ ናቸው ተብለው ከተቀመጡት አንዱ ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ነው። ይህም ከተማሪዎች የግል ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ ነው። ተማሪው በታላሚው ቋንቋ አዎንታዊ አተያይ፣የመማር ፍላጎት እና ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለው በፅሁፍና ንግግር ጊዜ ስህተቶች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች መካከል የአማርኛ ቋንቋ ድምጸ ልሳናት /ሆሄያት/ አጣጣል በትክክል ካለመረዳት የተነሳ የሚከሰት ስህተት እንደሆነ ይታሰባል። ይህም ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ እያሉ ሆሄያትን በትክክል ባለመለየታቸው ምክንያት አሁን ባሉበት ደርጃ ድርሰት ሲጽፉ በቃላት ግንባታ እና በአረፍተነገር ምስረታ ላይ ችግር ስላለ ሀሳባቸውን በአግባቡ በጽሁፍ ለመግለፅ በመቸገራቸው ምክንያት የስህተት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ተረጋግጧል።

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ላጋጠሟቸው ችግሮች አጥኚው የመፍትሄ ሀሳብ ይሆናሉ ብሎ ያስቀመጣቸው ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. በመማሪያ መፅሀፉ የቀረቡት ይዘቶች በአግባቡ ለማስተማር በቂ የሆነ ጊዜ ቢሰጥ፡፡
2. መምህራን የሰጧቸውን መልመጃዎች ብዙ ጊዜ ቢያርሙና ግብረ መልስ ቢሰጡ፡፡
3. ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ እያሉ የአማርኛ ቋንቋ ድምጸ ልሳናት /ሆሂያት/ በትክክል እንዲለዩ መምህራን የተለያዩ የማስተማር ስልቶችን በመጠቀም ቢያስተምሩ፡፡
4. ተማሪዎች የመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው ተፅዕኖ ያሳደረው የአማርኛ ቋንቋ የ12ኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ነው። በመሆኑም ለወደፊቱ ፈተናው የሚሰጥበት ሁኔታ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሁኔታዎችን ቢያመቻች፡፡
5. መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ ስለ ቋንቋው ጠቀሜታ አስፈላጊውን ግንዛቤ ቢሰጡ የሚሉትን አጥኚው እንደ መፍትሄ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ልዑልሰገድ አስፋው (1997) ። " በወላይተኛ እና በሲዳመኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (*ያልታተመ*)

ሰለሞን ሐለፎም (1997) ። *የድርሰት አፃፃፍ*። ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ።

ሰለሞን ዮህንስና ሌሎች (1994) ። *አማርኛን የማስተማር ስነዘዴ*፡፡(ሞጁዩል አንድ)፣አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት።

ስዩም ከበደ እና ሌሎች(1994)፡፡ አማርኛን የማስተማር ስነዘዴ፡፡ (ሞጁዩል አንድ)፣አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት።

የሻው ተሰማ (1996)፡፡ *ልሳነ-ብዕር ከመ ልሳነ ሰብእ*፡፡ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

*ያለው እንዳወቀ* (2006*)፡፡የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡* ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሊትማን መጻህፍት ድርጅት፡፡(3ኛ እትም)

ደብሬ ተሰማ (1990)። "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ፅሁበት ጊዜ የሚፍፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (*ያልታተመ*)

Ariningshi, D(2010). The effectiveness of using prefure service to improve the student's writing skill viewed from their learning motivation thesis education Sebelas Maret university.

Brougton, G & etal (1978). Teaching English as a foreign language, London, Routledge.

Brown, h.(1994). Principles of language learning & teaching. New Jersey; Prentice Hall regents.

Corder, S.P, (1981). ERROR analysis & inter-language. Oxford University Press.

Cresswell, J.W.(2010). Qualitative, quantitative and mixed approach: (2nd ED.). Thous and Oalcs: Cambridgme.

Dula y,H.M. Burt, S. Krashen. (1982). Language two. New York Oxford, Oxford University press

Dormmyie,z. (2007). research methods in applied linguistics; quantitative, qualitative and mixed methods. Oxford; Oxford University Press.

Eills (2008). The study of second language acquisition. Oxford, England; Oxford University Press.

Grass,s and sellinker, L.(2008). second language acquisition; an introductory course. Mahwah, Nj; eribaum .

Hasyim,s. (2002) Error analysis in teaching of Ethiopia English Journal of Petra, 42-50.

Hudson, G., (1976). High land east justice, in M.L.Bender (ed.) the non-Semitic languages in Ethiopia. pp.232-277. Michigan; Michigan State University.

James, C. (1998). Error in language learning and use; exploring error analysis; London; Longman.

James, C. (2013). error in language learning and use; exploring error analysis, Routledge.

Loot, D., (1983). analyzing & counteracting interference errors. ELT,Vol.37,no, p.p.253-261.

Loren F. Bliese (1981). Generative Grammar of Afar. Summer Institute of Linguistics, and the University of Texas at Arlington.

Negara, E, A. (1983). Non-constructive errors in African English; type and significance; No 2 . pp 35-45.

Nourish. H.J. (1983). language learners and their errors. London & Basing Stoke. Mcmillan Publishers Ltd.

Nourish. H.J. (1993). language learners and their errors. London & Basing Stoke. Mcmillan Publishers Ltd.

Richards (1974). perspectives on second language analysis London and New York, long man group UK limited.

Richards, J.C. (1974). Errors analysis perspectives on second language acquisition. London & New York; Long Man Group Limited.

Richards, J.C. & Schmidt, R (2002). Dictionary of language teaching & applied linguistics. London; long man.

Richards, J.C. & Schmidt, R, (2010). Long man Dictionary of language teaching & applied linguistics. ($4^{th}$ ED). Pearson Education Limited.

van patten, B. & Benati, A.G.(2010). Key terms in second language acquisition. London; Continuum International Publishing Group.

Werieesh,s,(1991). How to analyze inter-language journal of psychology & education. 9/1/,13-22

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ፡- ለተማሪዎች የቀረበ የጹሁፍ መጠይቅ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች

የዚህ መጠይቅ አላማ በአፋርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን የስህተት አይነቶች እና ምጮች ለመመርመር ለተጀመረው የድህረ ምረቃ ድግሪ ማሟያ ጥናት አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

መጠይቁም የተዘጋጀው በአፋር ክልል በዱብቲ እና ሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ከዚህ ጥናትም የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፅህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ እንቅፋት የሆኑባቸውን ነገሮች ለመቀነስ ብሎም ለማሰወገድ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእናንተ ቀና ትብብር ሲጨመርበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበህ/አንብበሽ/ ትክክለኛ ምላሽ እንድትሰጡኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜያችሁን በመሰዋት መጠየቁን በመሙላት ላደረጋችሁት ቀና ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ

1. በመጠየቁ ስም መፃፍ ተገቢ አይደለም፡፡
2. የመጠየቁን ምላሽ ከ3ኛ አይቶ መገልበጥ አይፈቀድም፡፡
3. ከምሰጡት መልሶች የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥና ብቻ የሚውል መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ መረጃ

1.1. ጾታ ______________________

1.2. እድሜ___________________

1.3. አፊ የፊታህበት/የፊታሽበት ቋንቋ_____________________________

1.4. አፍ ከፊታህበት/ከፊታሽበት ሌላ የምትናገረው/ዊ/ ቋንቋ ካለ_________________

1.5. ከቤተሰቦችህ/ሽ/ የምትግባበት/የምትግባቢበት/ቋንቋ________________________

1.6. ከወዳጅ ዘመድ ፡ከጓደኛ ጋር ደብዳቤ የምትፃፃፉበት/የምትፃፃፊበት ቋንቋ______________

<u>ክፍል ሁለት</u>

***መመሪያ አንድ***

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በጥቃቄ ካነበብክ/ሽ/በኃላ ተገቢ መልስ ይሆናል ብለህ/ሽ/ የምታስበውን/የምታስቢውን/ በተሰጠው ቦዶ ሳጥን ውስጥ የ "√" አስምጥ/ጭ/፡፡

1. በአፋርኛ ቋንቋ አፍህን /ሽን/ የፈታህ/ሽ/ ተማሪ እንደመሆንህ/ሽ/ በአማርኛ ቋንቋ የፅህፈት ክሂልን ለመማር ፍላጉት አለህ/ሽ/?

1.1. እጅግ በጣም □ 1.3. በመጠኑ □

1.2. በጣም □ 1.4. ፍላጉት የለኝም □

2. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልሱ 1.1 እና 1.2 ከሆነ ምክንያትህ /ሽ/ ምን ሊሆን ይችላል?

2.1. አብዛኛዎቹ የሀገራችን ታሪኮችና ስነ-ፅሁፎች በቋንቋ የተፃፉ በመሆናቸው አንብቤ ማስታወሻ እንዲያዝ የሚያስችል በመሆኑ፡፡ □

2.2. ተማሪዎች የፅሁፍ እውቀታቸውን የሚገልፅበት በመሆኑ ፡፡ □

2.3. አብዛኛዎቹ የሀገራችን ህዝቦች ቋንቋውን ስለሚችሉት ከነሱ ጋር በፅሁፍም ሆነ በንግግር በአማካኝነት ለመግባባት ስለሚረዳኝ ፡፡ □

2.4. የሰው ልጅ ሀሳቡን ሊገልፅበት ስለሚችል፡፡ □

3. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ ምላሽህ/ሽ/ 1.4 ከሆነ ምክንያትህ /ሽ/ምን ሊሆን ይችላል?

3.1. የአማርኛ ቋንቋ የሆሄያት ብዛትና ቅርፅ ስለሚያደናግረኝ፡፡ □

3.2. የአፍ ምፍቻ ቋንቋየ ጣልቃ እየገባ ስለሚስቸግረኝ፡፡ □

3.3. ድርሰት በምፅፍበት ጊዜ የቃላት እጥረት ስለሚገጥመኝ፡፡ 3.4. የስህፈት ስራ ውስብስብ በመሆኑ፡፡ □

4. የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ድርሰት እንድትፅፉ /እንድትለማመዱ/ መልመጃዎችን ይሰጧችኃል?

4.1. አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣሉ፡፡ ▫ 4.3. አልፎ አልፎ ይሰጣሉ፡፡ ▫

4.2 ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ፡፡ ▫ 4.4. በሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰጣሉ ፡፡

5. መምህራችሁ የሰጡትን መልመጃ ትሰራለህ/ትሰሪያለሽ/?

5.1. አብዛኛውን ጊዜ እሰራለሁ፡፡ ▫ 5.3. ከወር አንድ ጊዜ እሰራለሁ፡፡ ▫

5.2 አልፎ አልፎ እሰራለሁ፡፡ ▫ 5.4. ብዙውን ጊዜ አልሰራም፡፡ ▫

6. መምህራችሁ የሰጡትን የድርሰት መልመጃ ለእያንዳንዱ ተማሪ አርመው ይመልሳሉ?

6.1. ሙሉ በሙሉ አርመው ይመልሳሉ፡፡ ▫ 6.3. አልፎ አልፎ አርመው ይመልሳሉ፡፡

6.2. አብዛኛውን አርመው ይመልሳሉ፡፡ ▫ 6.4. አብዛኛውን ጊዜ አርመው አይመልሱም፡፡ ▫

7. በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/1.1 እና 1.2 ቢሆን የተፈጠሩ ስህተቶች አሉን?

7.1. እጅግ በጣም ▫ 7.3 በመጠኑ ▫

7.2. በጣም ▫ 7.4 ይህን ያህል አይደለም፡፡ ▫

8. በተራ ቁጥር 7 ለተሰጠው ጥያቄ ምላሽህ/ሽ/ 7.1 እና 7.2 ከሆነ መመህሩ/መምህርቷ/ የትኞቹ የስህተት አይነቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ?

8.1. የሆሄያት ቅርጽ (አጣጣል) ▫ 8.3. የአረፍትነገር አመሰራረት ▫

8.2. የቃላት አመራረጥ ▫ 8.4. የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም ▫

9. በአማርኛ ቋንቋ የሆሄያት ብዛትና ቅርፅ የተነሳ ለድርስት ፅሁፉ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራል ብለህ/ሽ/ትገምታለህ/ሽ/?

9.1. እጅግ በጣም ▫ 9.3. በመጠኑ ▫

9.2. በጣም ▫ 9.4. ምንም ተፅዕኖ የለውም ▫

10. በተራ ቁጥር 9 ለተጠየቀው ጥያቄ መላሽ 9.1 እና 9.2 ከሆነ ምክንያትህ /ሽ/ ምን ሊሆን ይችላል?

10.1 አልፎ አለፎ የሳድስና የሳልስየ ሆሄያት መመሳሰል ፡፡ ☐

10.2 የመደበኛእና ዲቃላ ሆሄያት ቅርፅ አለመለየት፡፡ ☐

10.3 ተመሳሳይ መጠሪያ ያለቸው ሆሄያት መኖር፡፡ ☐

10.4 ንበታቸው አስቸጋሪ የሆኑ ሆሄያት መኖራቸው፡፡ ☐

11. በፅህፈት ልምምድ ወቅት ለስህተት መፈጠር መንስኤ /ምንጭ/ይሆናሉ ብለህ/ሽ/ ያሰብከውን /ሽውን/ ነጥብ የትኛው ነው?

11.1. የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ድክመት ☐

11.2. የአማርኛ ቋንቋ ሆሄያት ብዛትና ቅርፅ ☐

11.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ☐

11.4. የአማርኛ ሰዋሰው ባህሪ አስቸጋሪነት ☐

12. ድርሰትን በመፃፍ በሚደረገው ልምምድ የትኛው ነጥብ ላይ ችግር ይገጥመሀል ወይም ይገጥምሻል?

12.1. የሆሄያት ድግፌት ላይ ☐

12.2. የቃላት አመራረጥ ላይ ☐

12.3. በአረፍተነገር አመሰራረት ላይ ☐

12.4. በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ☐

13. በፅህፈት ልምምድ ወቅት ተደጋጋሚ ስህተት የምትፈፅመው /የምትፈፅሚው ከቀረቡት አማራጮች መካከል በየትኛው ነው?

13.1. በሆሄያት ድግፌት ላይ ☐

13.2. በቃላት አመራረጥ ላይ ☐

13.3. በአረፍተነገር አመሰራረት ላይ ☐

12.4. በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ☐

14. በፃፋችሁት ድርሰት ውስጥ ስህተት ቢከሰት መምህሩ ምን አይነት እገዛ ያደርጋሉ?

14.1. በአብዛኛው ችግሩ የሚፈጠርበትን ነጥብ በመለየት ትኩረት እንዲሰጥ ያደረጋሉ፡፡ ◻

14.2. የተፈጠረውን ስህተት በድጋሚ ተማሪዎች አስተካክለው እንዲፅፉ ያደረጋሉ፡፡ ◻

14.3 ስህተት መፍጠር ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጥ ያደረጋል እንጅ ነውር እንዳልሆነ በተማዎች መካከል ግንዛቤ ይፈጥራሉ፡፡ ◻

14.4 በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭም የተለያዩ ድርሰቶችን እንዲናነብና አፃፃፋቸውን እንዲገነዘቡ ያበረታታሉ፡፡ ◻

## መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢ መልስ ይሆናል ብለህ /ሽ/ያሰብከውን /ያሰብሽውን/ መመዘኛ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የ "√" ምልክት አስቀምጥ/ጭ/

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| 1 | በአማርኛ ቋንቋ  ፅህፈትን መማር ያለህ/ሽ/ፍላጎት ምን ያህል ነው ? | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ድርሰት ለመፃፍ ለምታደረጉት ልምምድ ምን ያህል መልመጃዎችን ይሰጧችኃል? | | | | |
| 3 | በተማሪዎች የተፃፈ መልመጃዎች በመምህሩ መታረማቸው ለፅህፈት ትምህርት ፋይዳ ይኖረዋል? | | | | |
| 4 | የተሰሩት መልመጃዎች በመምህሩ ታርመው ሲመለሱ ምን ያህል ስህተቶች ተገኝተዋል? | | | | |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ በሆሄያት ቅርፅና ብዛት የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶች መጠን ምን ያህል ነው? | | | | |
| 6 | ተማሪዎችን ድርሰት በማለማመድ እረገድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እገዛ ያደርጋሉ? | | | | |
| 7 | በምትማርበት/በምትማሪበት የክፍል ደረጃ ያለው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ጽህፈትን ለማለማመድ ጠቀሜታ አለው? | | | | |

## ክፍል ሶስት

***መመሪያ***

***በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች የተማሪውን ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎቹን በጥሞና ከአነበብክ/ሽ/በኃላ ተገቢ ናቸው ብለህ/ሽ/ ያሰብከውን /ያሰብሽውን/ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ አብራርተህ /አብራርተሽ ፃፍ/ፃፊ/፡፡***

***1. ድርሰትን ለመፃፍ በምትሞክርበት/ በምትሞክሪበት ጊዜ ለስህተት የሚያጋልጡ/ የሚጋልጡሽ/ የስህተት ዓይነቶችን ዘርዝር/ዘርዝሪ/?***

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

________________________________________________________________________::

***2.ድርሰትን ለመፃፍ እንዳትነሳሳ /እንዳትነሳሽ/ እንቅፋት የሆነብህ/ሽ/ ነጥቦችን ዘርዝርህ/ሽ/ፃፍ/ጻፊ/?***

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

________________________________________________________________________::

3. ድርሰትን ለመፃፍ በምታደረገው /ዊ/ልምመድ ወቅት ለስህተት ይዳርጉኛል ብለህ/ሽ/ያሰብከውን /ያሰብሽውን/ የስህተት ምንጮች ዘርዝር/ዘርዝሪ/?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________::

4.አንተ /አንች/ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ እንደመሆኑ የአማርኛን የፅህፈት ትምህርት በተመለከት የሚኖርህ /የሚኖርሽ/አወንታዊ እና አሎታዊ አመለካከትህን/ሽ/ በሰፊው አብራርተህ /ሽ/ፃፍ/ፃፊ/?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________::

## አባሪ ለ፦ ለመምህራን የቀረበ የፁሁፍ መጠይቅ

## የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

**በ2ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ ፅሁፋዊ መጠይቅ**

የተከበራችሁ መምህራን

የዚህ መጠይቅ አላማ አፋቸውን በአፋርኛ ቋንቋ የፈቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች እና የስህተቶቹን ምንጮች በመመርመር መፍተሁዎችን ለመጠቆም ለተጀመረው የድህረ ምረቃ ድግሪ ማሚያ ጥናት አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፅህፈትን በሚማሩበት ጊዜ እንቅፋት የሆኑባቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ እንኳ ባይሁንም በተወሰነ መልኩ ለመቀነስ እና ለማስወገድ እገዛ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእናንተ ቀና ትብብር ሲጨመርበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብባችሁ እና በአግባቡ ሞልታችሁ እንድትሰጡኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

በመጨረሻም ውድ ጊዜችሁን በመሰዋት መጠየቁን በመሟላት ላደረጋችሁት ቃና ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

## ክፍል አንድ

<u>አጠቃላይ መመሪያ፡-</u> ተገቢ የሆነውን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይሙሉ፡፡

1.1. ጾታ______________

1.2. የትምህርት ደረጃ________________________________________________

1.3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘረፍ_____________________________________

አብይ________________________________________

ንዑስ________________________________________

1.4 . የአገልግሎት

ዘመን_______________________________________________

1.5 . በዚህ ትምህርት ቤት ያሉዎት የማስተማር

ልምድ_______________________

1.6 . የሚስተምሩበት የክፍል

ደረጃ________________________________________

1.7. በተመደቡበት የክፍል ደረጃ በሳምንት የሚስተምሩት ክፍል ጊዜ ብዛት

## መመሪያ አንድ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሠጡት አማራጮች መካከል ተገቢ ነው ብለው ያሰቡትን መልስ ብቻ በመምረጥ በተሰጠው ሣጥን ውስጥ የ"√" ምልክት ያስቀምጡ፡፡

1. በአፋርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ የፅህፈት ክሂልን ሲማሩ ፍላጎት አላቸው?

1.1 እጅግ በጣም ◻ 1.3 በመጠኑ ◻

1.2 በጣም ◻ 1.4 ፍላጎት የላቸውም ◻

2. በተራ ቁጥር '1' ለተጠየቀው ጥያቄ መልሰዎ 1.1 እና 1.2 ከሆነ በተማሪዎቻችሁ ድርስት የመፃፍ ልምምድ ወቅት እገዛ ታድርጋለችሁ?

2.1 እጅግ በጣም ◻ 2.3 በመጠኑ ◻

2.2 በጣም ◻ 2.4 አልፎ አልፎ ◻

3. በተራ ቁጥር "2" ለተጠቀው ጥያቄ መልሰዎ 1.1 እና 1.2 ከሆነ ተማሪዎችን በምን አይነት መንገድ እገዛ ያደርጋሉ?

3.1. ድርስት የመፀፍ ፍላጎት እንዲኖራቸው በተማሪዎች መካከል ግንዛቤ በመፍጠር፡፡ ◻

3.2. ድርስት እንዲፅፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ፡፡ ◻

3.3. የተለያዩ ድርሰቶችን በክፍል ውስጥም ሆነ በክፍል ውጭ እንዲያነቡ በማድረግ፡፡ ◻

3.4. ተማሪዎች ድርሰትን ለመፃፍ ከመሞከራቸው በፊት ስለአፃፃፉ ገለፃ ማድረግ፡፡ ◻

4. ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የሚያግዛቸው ልምምድ እንዲያደርጉ የሚያግዛቸውን መልመጃዎች ይሰጣሉ?

4.1. አብዛሀኛውን ጊዜ እሰጣለሁ፡፡ ◻ 4.3. አልፎ አልፎ እሰጣለሁ፡፡ ◻

4.2. ብዙ ግዜ እሰጣለሁ፡፡ ◻ 4.4. በሁለት ወር አንድ ጊዜ እሰጣለሁ ◻

5. ተማሪዎች የተሰጣቸውን ጽሁፋዊ መልመጃዎች ሰርተው ይመጣሉ?

5.1. አብዛሀኛውን ጊዜ ◻ 5.3. አልፎ አልፎ፡፡ ◻

5.2. ብዙ ጊዜ፡፡ ◻ 5.4. አብዘሃኛውን ጊዜ፡፡ ◻

6. ተማሪዎች የሰሩትን መልመጃዎች በወቅቱ አርመው ይመልሳሉ?

6.1. ሙሉ በሙሉ አርሜ እመልሳለሁ፡፡ ◻

6.2. የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች አርሜ እመልሳለሁ፡፡ ◻

6.3. አልፎ አልፎ ተማሪዎች አርሜ እመልሳለሁ ፡፡ ◻

6.4. አብዛኛውን ጊዜ አርሜ አልመልስም፡፡ ◻

7. በተራ ቁጥር 6 ለተጠየቀው ጥያቄ መልሰዎ 6.1 እና 6.2 ከሆነ ተማሪዎች የሰሩት ስህተት አለ?

7.1. እጅግ በጣም ◻ 7.3. በመጠኑ ◻

7.2. በጣም ◻ 7.4. ይሄን ያህል አይደለም ◻

8. በተራ ቁጥር 7 ለተሰጠው ጥያቄ ምላሽዎ 7.1 እና 7.2 ከሆነ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የፈፀሙት ስህተት ምን አይነት ነው?

8.1. በሆሂያት ግድፈት ላይ ◻ 8.3. በአረፍተነገር አመሰራረት ◻

8.2. በቃላት አመራረጥ ላይ ◻ 8.4. በስርዓት ነጥብ አጠቃቀም◻

8.5. ከእነዚህ ከተገለጹት የተለየ ከሆነ በጽሁፍ ቢገለጽ ----------------------------------------

9. ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ስህተት የሚሰሩ ከሆነ ለስህተቶቻቸው ምክንያት ይሆናሉ ብለው ከሚገምቷቸው ጉዳዮች መከካል ቀዳሚው የትኛው ነው ብለው ያስባሉ?

9.1. የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ድክምት ◻

9.2. የአማርኛ ቋንቋ ሆሂያት ቅርፅ (አጣጣል) ◻

9.3. የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪነት ◻

9.4. ከእነዚህ ከተገለጹት የተለየ ከሆነ በጽሁፍ ቢገለጽ --------------------------------------

10. በተራ ቁጥር 9 መልሰዎ 9.1 ከሆነ የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ድክምት የመነጨው በምን ሁኔታ ነው ብለው ይገምታሉ?

10.1. ምቹና ማሪኪ የሆነ የመማሪያ ክፍል አለመኖር፡፡ ◻

10.2. በድካምና በሰውነት መዛል ፡፡ ◻

10.3. የመምህሩ የትምህርት አቀራረብና አነጋገር ግልፅ አለመሆን፡፡ ◻

10.4. ተማሪዎች ድርስትን ለመፃፍ ያላቸው ተነሳሽነት አናሳ መሆን፡፡ ◻

10.5. ከእነዚህ ከተገለጹት የተለየ ከሆነ በጽሁፍ ቢገለጽ ------------------------------------

11.የተራ ቁጥር 10 ምላሽዎት 10.4 ከሆነ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ?

11.1. ምቹና ሳቢ የመማሪያ ክፍል አለመኖር፡፡ ◻

11.2. የቋንቋ ችሎታ ማነስ፡፡ ◻

11.3. የማሪዎቹ ግዴለሽነት ◻

11.4. የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት አስቸጋሪነት ◻

11.5. ከእነዚህ ከተገለጹት የተለየ ከሆነ በጽሁፍ ቢገለጽ -----------------------------------

12. አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማር ተማሪ በቋንቋው በቀላሉ ማንበብ እና መፃፍ ይሳካታል ብለው ይገምታሉ?

12.1. እጅግ በጣም ◻

12.2 በጣም ◻

12.3. በመጠኑ ◻

12.4. ሊሳካለት አይችልም ◻

13. በተራ ቁጥር 12 ለተሰጠው ጥያቄ መላሽዎት 12.3 እና 12.4 ከሆነ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?

13.1. የመደበኛ እና ዲቃላ ሆሄያትን ቅርፅ በቀላ አለመለየት፡፡ ◻

13.2. የአማርኛ ቋንቋ ድምፆች /ሆሄያት/ ◻

13.3. ሞክሼ /ተመሳሳይ/ መጠሪያ ያላቸው ሆሄያት መኖራቸው ◻

13.4. ንበታቸው አስቸጋሪ የሆኑ ሆሄያት መኖራቸው፡፡ ◻

14. በ12ኛ ክፍል ያለው የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መፀሀፍ ፅህፈትን ለማለማመድ ጠቀሜታ አለው ብለው ያስባሉ?

14.1. እጅግ በጣም ◻

14.2 በጣም ◻

14.3 በመጠኑ ◻

14.4 ብዙም የለውም ◻

15. በተራ ቁጥር 14 ለቀረበው ጥያቄ መላሽዎት 14.1 እና 14.2 ከሆነ ተማሪዎቹ ፅህፈትን በተሻለ ሁኔታ እንዲለማመዱ የሚያደርጓቸው መልመጃዎች የትኞቹ ናቸው?

15.1. ክፍል አንድ ◻

15.2. ክፍል ሁለት ◻

15.3. ክፍል ሦስት ◻

15.4. ክፍል ሁለትና አምስት ◻

## መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ከጥያቄዎቹ ትይዩ ከቀረቡት መመዘኛዎች መካከል ተገቢ የሆነውን መልስ በመምረጥ በሳጥኑ ውስጥ የ"√" ምልክት አስቀምጡ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| 1 | በአፋርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ የፅህፈት ክሂልን ሲማሩ ያላቸው ፍላጉት ምን ያህል ነው? | | | | |
| 2 | ተማሪዎች ድርሰትን እንዲፅፉ /እንዲለማመዱ/ ምን ያህል እገዛ ያደርግሉ? | | | | |
| 3 | ተማሪዎች ድርስትን በመፃፍ ሂደት ላይ በሚያደረጉት ሙከራ የሚፈፅሙት የስህተት መጠን ምን ያህል ነው? | | | | |
| 4 | አሁን በምታስተምሩበት የክፍል ደረጃ ያለው የማስተማሪያ መፀሀፍ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች ፅህፈትን በማለማመድ በኩል ምን ጠቀሜታ አላቸው? | | | | |
| 5 | በጽሁፍ ልምምዱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለው ተጽዕኖ ምን ያህል ነው? | | | | |

## <u>ክፍል ሶስት</u>

### <u>*መመሪያ ሶስት፡-*</u>

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች የእርስዎን ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም በስራ ሂደት ካጋጠመዎ ተሞክሮና ልምድ በመነሳት ተገቢ መልስ ይሆናሉ ብለው የገመቱትን ሀሳብ በጽሁፍ እንዲመልሱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

1. በአፋርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ የፅህፈት ክሂል ትምህርት ላይ ያላቸው

አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ስባሉ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________::

2. አሁን የምታስተምሩበት መፅሀፍ የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማሻሻል ፋይዳው ምን ያህል እንደሆነ ቢያብራሩልኝ?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________::

3. እርስዎ የተማሪዎችን መልመጃዎች ሲያርሙ የገጠመዎት ችግር ካለ ይግለፁልኝ?

________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
______________::

4. ተማሪዎች ድርሰትን በሚለማመዱበት ጊዜ የሚፈፅሙት የስህተት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
____________________________________________________________________::

5. ተማሪዎች ድርሰት በመፃፍ በሚያደርጉት ልምምድ ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚፈፅሟቸው
የስህተት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው?

________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
____________________________________________________________________::

6. ተማሪዎች ድርሰትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምንጮች/መንስኤዎች/ ናቸው ብለው ያሰቡትን ይዘርዝሩ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________::

7. እርስዎ የአማርኛ ቋንቋ መምህር እንደመሆኑዎ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የአፋርኛ ተማሪዎች የፅህፈት ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ ሊደረጉላቸው ይገባሉ ብለው ያሰቡትን ሀሳብ ይፃፉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________::

## አባሪ ሐ ፡ ለተማሪዎች የቀረበ የድርሰት መልመጃ

የሂዩማኒተስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድርሰት መልመጃዎች

ክፍል አንድ

*ሀ. መመሪያ አንድ*

1. ድርሰት በሚፃፍበት ወረቀት ላይ ስም አይጻፍም፡፡
2. ከንደኛ መኮረጅ አይፈቀድም፡፡

*ለ. መመሪያ ሁለት*

ከዚህ በታች ከተሰጡት ርዕሶች መካከል ብዙ ያፅፈኛል የምትለውን/የምትይውን/ አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ ከአንድ ገፅ ያላነሰ ድርሰት በክፍል ውስጥ ፃፍ/ፊ/፡፡

ድርሰቱን ለመፃፍ የተሰጠው ጊዜ 1፡00 (አንድ ሰአት) ብቻ ነው፡፡

1. ባለፉት ሁለት ተከታታይ አመታት በሀገራችን በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት ብዙ ህዝብ ጉዳት ደርሶበታል፤ ብዙ ንብረትም የወደመ መሆነን አይታችኃል፤ በመገናኛ ብዙሃንም ሰምታችኃል፡፡ ስለሆነም አንተ/ቺ/ ይህን ችግር መነሻ በማድረግ <u>**ጦርነት የሚያስከተለው ችግር**</u> በሚል ርዕስ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
2. በሃገራችን ሰዎች እድሜያቸው ለትዳር ሲደርስ ከሚወዱት ሰው ጋር በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ በጋብቻ ስርአት ትዳር መስርተው ሂወታቸውን መምራት የተለመደ ነው፡፡ በመሆኑም <u>**የአፋር ብሄረሰብ ባህላዊ ጋብቻ**</u> በሚል ርዕስ አንድ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
3. በኢድ በአል አከባበር ሰሞን የሚታየውን ድባብ በማስታወስ የኢድ በአል ዝግጅት በሚል ርዕስ ሃሳብህን/ሽን/ በፅሁፍ አቅርብ/ቢ/፡፡
4. መምህር/መምህርት/ ብትሆን/ብትሆኚ/ ለተማሪዎችህ/ሽ/ ልታደርግላቸው የሚገባህን/ሽን/ ነገር በማሰብ <u>**መምህር ብሆን ኑሮ**</u> በሚል ርዕስ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
5. ትምህርት ለሰው ልጅ የሚሰጠው ጥቅም በጣም ብዙ ነው፡፡ ስለሆነም የትምህርት ጥቅም በሚል ርእስ ሃሳብህን/ሽን/ በፅሁፍ ግለጭ፡፡

# ክፍል ሁለት

***ሀ. መመሪያ አንድ***

1. ድርሰት በሚፃፍበት ወረቀት ላይ ስም አይጻፍም፡፡
2. ከንደኛ መኮረጅ አይፈቀድም፡፡


***ለ. መመሪያ ሁለት***

ከዚህ በታች ከተሰጡት ርዕሶች መካከል ብዙ ያፅፈኛል የምትለውን/የምትይውን/ አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ ከአንድ ገፅ ያላነሰ ድርሰት በክፍል ውስጥ ፃፍ/ፊ/፡፡


ድርሰቱን ለመፃፍ የተሰጠው ጊዜ 45 ደቂቃ ብቻ ነው፡፡

1. በአሁኑ ጊዜ በአካባቢያችን ብዙ ሰዎች በተለይ ወጣቶች በተለያዩ ሱሶች ተገዥ በመሆን ህይወታቸውን በትክክል መምራት አልቻሉም፡፡ ስለሆነም አንተ/ቺ/ይህ ሱስ ያስከተለውን ጉዳት በመገንዘብ **<u>ጫት እና መዘዙ</u>** በሚል ርዕስ አንድ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
2. በሀገራችን በአሁኑ ሰአት ድርቅ ባስከተለው ቸፍግር ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች ጉዳት እንደ ደረሰ በመገናኛ ብዙሃን እየሰማችሁ ነው፡፡በመሆኑም ይህን በመገንዘብ **<u>የድርቅ አስከፊነት</u>** በሚል ርዕስ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
3. አንተ/ቺ/ ባለሃብት ብትሆን/ኚ/ በአካባቢው ማህበረሰብ ልታደርገው/ጊው/ የሚገባህ/ሽን/ ነገር በማሰብ **<u>ባለሃብት ብሆን</u>** …..በሚል ርዕስ አንድ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡
4. በአፋር ብሄረሰብ የጎሳ ተጠሪዎችን ሚና ለማያውቅ እንግዳ ሰው ይህን ለማስረዳት ቢፈለግ፣ እንዴት ልትገልፅለት/ጭለት/ እንደምትችል/ችይ/ በማሰብ **<u>የጎሳ ተጠሪዎች</u>** ሚና በሚል ርዕስ አንድ ፅሁፍ ፅፈህ/ሽ/ አቅርብ/ቢ/፡፡
5. የዳጉ ስርአት የሚሰጠው ጥቅም እንዳለ ሁሉ ጉዳትም ይኖረዋል፡፡ ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት **<u>የዳጉ ስርአት ጥቅምና ጉዳት</u>** በሚል ርዕስ በማነፃፀር አንድ ድርሰት ጻፍ/ፊ/፡፡


**አባሪ መ፦ ለቋንቋ አጠቃቀም የቀረበ የስህተት ምሳሌ**




## አባሪ ሠ፡ ለቋንቋ አወቃቀር የቀረበ የሥህተት ምሳሌ



**አባሪ ረ፡- ለስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ቀረበ የስህተት ምሳሌ**



## አባሪ ሰ፡- መለየት ያልተቻሉ የስህተት ምሳሌ



**ማረጋገጫ**

እኔ ከዚህ በታች ስሜና ፊርማዬ የተጠቀሰው የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን እና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ጽሑፎች በሙሉ በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________

ፊርማ ____________________